# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 157 የካቲት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - ሀዳስ አብርሀ

## የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን ለመፍታት የተጀመረውን ጥረት ለማሳካት ኢትዮጵያ የድርሻዋን ትወጣለች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን ለመፍታት የተጀመረውን ጥረት ለማሳካት ኢትዮጵያ የድርሻዋን ትወጣለች ሲሉ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ገለፁ።

44ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚዎች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በትላንትናው ዕለት በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።

በስብሰባው መክፈቻ ላይ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን ለመፍታት የተጀመረውን ጥረት ለማሳካት ኢትዮጵያ የድርሻዋን ትወጣለች።


የአፍሪካን ችግር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ፎቶ - ሀዳስ አብርሀ

## “በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ የልማት ግቦችን ለማሳካት የኅብረቱ አባል ሀገራት በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል”

\- ሙሳ ፋኪ መሃመት
የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር

**ቃልኪዳን አሳዬ እና ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራት በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል ሲሉ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሃመት ገለጹ።

44ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈፃሚዎች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በትናንትናው ዕለት ተጀምሯል።

የኅብረቱ የሥራ አስፈፃሚዎች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ መክፈቻ ላይ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሃመት እንደገለጹት፤ አፍሪካውያን በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ አካታችና ዘላቂ ልማት ግቦች ለማሳካት በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል።

የምንመኛትን አፍሪካ ዕውን ለማድረግ፤


“በአጀንዳ 2063 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)

## ኢትዮጵያውያን ኅብረ ብሔራዊነታቸውን በዓድዋ ድል አስመስክረዋል

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ኅብረ ብሔራዊነታቸውን ጠላትን በአንድነት ቆመው ተዋግተው ባሸነፉበት የዓድዋ ድል ማስመስከራቸውን ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ሕዝቦች ሀገራቸውን ለማዳን በመዘጋጀታቸው፣ በአንድነት በተከፈለ መስዋዕትነት የተመዘገበ የሚያስደንቅና በአርዓያነትም


ኢትዮጵያውያን ኅብረ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የሐሮማያ ሐይቅ ተስፋና ስጋት

**ጌትነት ምሕረቴ**

አካባቢው ማራኪ ነው፡፡ በሐሮማያ ሀይቅ ዙሪያ ያሉ እርሻዎች አካባቢውን አረንጓዴ ስጋጃ የተነጠፈ አስመስለውታል፡፡ የአዕዋፋት ድምፅ፣ የጀልባዎች ቀዘፋና የአካባቢው ሥነ ምሕዳር የጎብኝዎችን ቀልብ ይስባል፡፡

በ1996 ዓ.ም ሐይቁ በዓይናችን እያየነው ደረቀ የሚለው ሐሮማያ ሐይቅ አጠገብ በምትገኘው ማያ ከተማ ተወልዶ ያደገው አቶ ረመዳን አሊ፤ በወቅቱ ሐይቁ ሲደርቅ እናትና አባታችንን እንዳጣን ሁላችንም የአካባቢው ነዋሪዎች አዘንን፣ ተከፋን፣ ዳግመኛም ሐይቁ ይመለሳል ብለንም አላሰብንም ይላል፡፡

የአምላክ ሥራ አይታወቅም፤ ያልገመትነው ነገር ተከሰተ፡፡ ሐሮማያ ሐይቅ ከ17 ዓመታት በኋላ ተመልሶ መጣ፡፡ እኛም ዳግም እንደተወለደ ሰው ተደሰትን፣ ጨፍርን፣ እንደ ዓይናችን ብሌን የምናየውን ሐይቅ በደስታ እንባ ተቀበልነው ብሏል፡፡


የሐሮማያ ሐይቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










## “በዓውደርዕዩ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የትውልድ ቅብብሎሽ እንዳለው ታይቷል”

- አምባሳደር አሚን አብዱልቃድር

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን በሚል የተዘጋጀው ዓውደርዕይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የትውልድ ቅብብሎሽ እንዳለው የሚያሳይ መሆኑን በካናዳ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የዲያስፖራ ዘርፍ ኃላፊ አምባሳደር አሚን አብዱልቃድር ገለጹ ።

አምባሳደር አሚን አብዱልቃድር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዓውደርዕዩ በየዘመናቱ የተሠሩ ኢትዮጵያ ታሪኮች ተተንትነው የቀረቡበት ነው። ይህ የቀድሞውን የአሁኑንና የወደፊቱን የያዘ ዓውደርዕይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሂደቱ የትውልድ ቅብብሎሽ እንዳለው ያሳየ ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ለዓለም፣ ለአፍሪካ ብሎም ደግሞ ለጥቁር ሕዝቦች ያበረከተችው ዘርፈ ብዙ እሴቶች አሏት። በዚህም ኢትዮጵያ ለዓለም የዲፕሎማሲ መንደር መሆን ችላለች ፡፡ በዓውደ ርዕዩም የታየው ይህ መሆኑን ገልጸዋል።

በሃገራችን ከለውጡ በኋላ አንጸባራቂ ለውጦች እያስመዘገበችበት ያለችበት ወቅት ነው ያሉት አምባሳደር አሚን፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ብልጽግና ማዕከል የምትሆንበትን እድሎች እየተፈጠሩላት መሆኑ በሃገሪቱ እየተገነቡ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ማሳያ መሆናቸውን ተናግረዋል።

እነዚህ ፕሮጀክቶችም ከማኅበረሰቡ አልፎ ኑሮዋ ቸውን በኢትዮጵያ ላደረጉ የሌላ ሃገር ዜጎችም ምቹ አጋጣሚ የተፈጠረበት ጊዜ መሆኑን በመጥቀስ፤ ከዛም ባለፈ ፕሮጀክቶቹ ኢትዮጵያ የታሪክ እና የሥልጣኔ ምንጭ መሆኗን አጉልቶ እንዳወጣ አስረድተዋል።

አምባሳደር አሚን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመሆን ያዘጋጀው ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን ዓውደርዕይ ብዙ ታሪኮችን በአግባቡ ተሰንደው ለትውልዱ እንዲሁም ለማኅበረሰቡ የቀረበበት አግባብ የሚያስደንቅ ነው። በዚህም ዲፕሎማሲ ምን ማለት እንደሆነና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ምን ላይ እንደሚገኝ የሚያሳይ መሆኑን አብራርተዋል።


# በግማሽ ዓመቱ በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓቱ የ103 ቢሊዮን ብር ግዢ ተፈፅሟል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው ግማሽ በጀት ዓመት የ103 ቢሊዮን ብር ግዢ በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት መፈፀሙን በኢፌዲሪ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ። ባለሥልጣኑ 169 የፌደራል ተቋማት ዘመናዊ የግዥ አሠራር እንዲከተሉ ማድረጉንም ገልጿል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሐጂ ኢብሳ እንዳሉት፤ 63 በመቶ የሀገሪቱ በጀት ለግዢ ይውላል። ይህ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣበት የግዢ ሂደት ዘመናዊ የቁጥጥር አሠራር ተዘርግቶለት እየተተገበረ ይገኛል። በስድስት ወራት ውስጥ የ103 ቢሊዮን ብር ግዢ በዘመናዊ ግዢ ሥርዓት እንዲፈፀም ተደርጓል።

ይህ ሲስተም መኪኖች በቀን ምን ያህል ነዳጅ እንደተጠቀሙ በዝርዝር የሚያሳይ ሲሆን፤ ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ መንቀሳቀስ ሲሞክር የሚጠቁም አላርም ወይም ደወል እንደተገጠመላቸው ጠቅሰዋል። አላስፈላጊ ወጪ ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያም እየተዘረጋ እንደሆነ ገልፀዋል።



**አቶ ሐጂ ኢብሳ**

የኤሌክትሮኒክስ ግዢ አሠራር ውጤታማ እንዲሆን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ምሑራን ጥናት እንዲያጠኑ መደረጉን በመግለፅ፤ ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ተቋማት ለመሸለም ዕቅድ መያዙን ተናግረዋል።

የግዥ ሥርዓቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተተገበረ አሠራር ከመሆኑ አንፃር የቴክኒክ ችግሮች እንደነበሩበት የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ እንዲሠራ ከማስቻል አኳያ የሲስተም መቆራረጥ እና የልምድ ማነስ ችግሮች ተጠቃሽ እንደሆኑ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሐጂ ገለፃ፤ ትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙ አራቱም ዩኒቨርሲቲዎች በዘመናዊ ሲስተም ግዢ እንዲካተቱ ተደርገዋል። ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ወደ አሠራሩ ለማስገባት እየተሠራ ነው። በተመሳሳይ ድሬዳዋ፣ ባቱ እና አፋር በተያዘው ሳምንት አሠራሩን የመዘርጋት ሥራዎች ይጀምራሉ።

ዘመናዊ የግዥ ሂደት ለመዘርጋት በክልሎች አካባቢ የፀጥታ ጉዳይ፣ የኢንፍራስትራክቸር ችግር እንዲሁም የሠለጠነ የሰው ኃይል እንቅፋት እንደፈጠሩ አመልክተዋል። የአሠራር ሥርዓቱ ከተለያየ ጉዳት እንዳያስከትል በበላይነት የሚቆጣጠረው የኢንፎርሜሽን ደህንነት መረብ አስተዳደር እንደሆነ ጠቁመዋል።

# በዞኑ ከ3 ነጥብ 6 ቢሊዮን በላይ ብር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል

**ውብሸት ሰንደቁ**

ሶዶ፡- በዞኑ ከ3 ነጥብ 6 ቢሊዮን በላይ ብር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ፈቃድ መሰጠቱን የወላይታ ዞን አስተዳደር አስታወቀ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ የማይገቡ ኢንቨስተሮች ለልማት የተሰጣቸውን መሬት እንደሚነጠቁ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙዔል ፎላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ በዞኑ ከ3 ቢሊዮን 680 ሚሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ኢንቨስትመንቶች ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህ ኢንቨስትመንቶች ፈቃድ እንዲያገኙ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ ተሠርቷል፡፡

ፈቃድ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 53 የሚደርሱ መሆናቸውን የተናገሩት አስተዳዳሪው፤ ከኢንቨስትመንቶቹ ውስጥ ወደሥራ የገቡ እና በሂደት ላይ የሚገኙ ስለመኖራቸውም አብራርተዋል፡፡

ወደ ዞኑ የሚፈሰው የኢንቨስትመንት ፍላጎት ከዓምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ኢንቨስትመንቶቹ በገጠር እርሻ፤ በከተማ አገልግሎት ዘርፍ፣ በአነስተኛና መካከለኛ አምራች እና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ጭምር የተሠማሩ ናቸው ሲሉም ገልጸዋል፡፡ የአካባቢው ተወላጅ ዲያስፖራዎች አብዛኛውን የኢንቨስትመንት ክፍል እንደሚሸፍኑም ነው የጠቀሱት፡፡

ቀደም ሲል በኢንቨስትመንት ስም መሬት ወስደው አጥረው ያስቀመጡ ባለሀብቶች በዞኑ እንደነበሩ የተናገሩት አቶ ሳሙዔል፤ በነዚህ ላይ አስፈላጊው ክትትል እና ርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ ነው የተናገሩት፡፡

ባለፈው ዓመት የኢንቨስትመንት መሬት ወስደው አጥረው ያስቀመጡ እና ወደሥራ ያልገቡ 19 ኢንቨስተሮችም ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል ብለዋል፡፡

ኢንቨስተሮቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ የማይገቡ ከሆነ መሬቱን ይነጠቃሉ ሲሉም አስጠንቅቀዋል፡፡

ወደሥራ የገቡ ባለሃብቶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑና የፈጠሩት የሥራ ዕድል እና የዋጋ መረጋጋት ላይ ተደጋጋሚ ውይይቶች እየተደረጉ እንደሚገኝ እና ውጤታማነት ላይ ያተኮረ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማድረግ ዝግጅት መደረጉንም አክለው አብራርተዋል፡፡

ኢንቨስተሮች ያስመዘገቡት ካፒታል መሬት ላይ ወርዶ በትክክል ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን መፍታት የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡



**አቶ ሳሙዔል ፎላ**

በዞኑ በአብዛኛው የተማረ ከፍተኛ የሥራ አጥ ቁጥር መኖሩን የጠቀሱት አስተዳዳሪው፤ ይህ በመንግሥት በኩል ብቻ ሊፈታ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ኢንቨስትመንቶችን ወደ ሥራ በማስገባት ጭምር የግሉ ዘርፍ የሥራ አጥ ቁጥርን የመቀነስ ሚናውን እንዲወጣ ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# የወጣቶችን የኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ለመቀነስ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የወጣቶችን ለኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ለመቀነስ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ተገለጸ።

በጤና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና የጤና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት ዶክተር ተገኔ ረጋሳ ዓለም አቀፍ የኮንዶም ቀን መከበርን አስመልክተው እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ የቫይረሱን ስርጭት በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ባለፉት ዓመታት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም ከሦስት ነጥብ አምስት በመቶ በላይ በመድረስ ወረርሽኝ ደረጃ ላይ የነበረውን ስርጭት ወደ ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ ማውረድ ተችሏል።

ነገር ግን ዛሬም ቢሆን በወጣት ሴተኛ አዳሪዎችና ተማሪዎች ላይ ያለው የስርጭት መጠን 18 ነጥብ ሰባት በመቶ እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር ተገኔ፤ ስርጭቱም በከተሞች ትልቁን ድርሻ ይይዛል ብለዋል።

በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች በተለያዩ የአባላዘር በሽታዎች የሚያዙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘውም ኤች አይ ቪ መሆኑን ጠቁመዋል።

በመሆኑም ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ሥራዎችን በመሥራት ስርጭቱን ለመግታት እየተሠራ መሆኑን በመጥቀስ፤ ከመከላከል ሥራው በተጓዳኝም ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው




ከስድስት መቶ ሺ በላይ የሚሆኑ ዜጎችንም የሕክምናው ተጠቃሚ የማድረግ ሥራዎችም ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል ብለዋል።

ዛሬም ድረስ ስለ ኤች አይ ቪ ተጋላጭነት በወጣቶች በኩል ግንዛቤው ቢኖርም በትግበራ ረገድ ክፍተት ያለ በመሆኑ የባሕሪ ለውጥ እንዲፈጠር ከፍተኛ ሥራ መሥራት ይጠበቃል ያሉት ዶክተር ተገኔ፤ በተለይም ኮንዶምን በመጠቀም ረገድ የሚታየው ቸልተኝነት ለቫይረሱ መስፋፋት ትልቅ ድርሻ ያለው በመሆኑ ለማስተካከል ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ተገኔ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የቫይረሱን ስርጭት በመግታት እ.አ.አ በ2030 ኤድስ የማኅበረሰቡ




የጤና ችግር ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የያዘችውን እቅድ ለማሳካት ኮንዶም ትልቅ ሚና አለው። በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት ሀምሳ አምስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኮንዶም ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ጥራቱ ተፈትሾ እየተሰራጨ ይገኛል።

በዚህ ረገድ ከመንግሥት ጎን በመቆም የኮንዶም ተደራሽነት በነፃ እንዲዳረስ የሚሠሩ እንደ ኤ. ኤች.ኤፍ ያሉ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ተሳትፎም ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ጠቁመዋል።

የኤ ኤች. ኤፍ በኢትዮጵያ የፕሮግራም ዳይሬክተር ዶክተር መንግሥቱ ገብረ ሚካኤል በበኩላቸው የወጣቶች የኤች.አይ. ቪ. ተጋላጭነት አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህንን ችግር በመቅረፍ የነገ ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን ጤና ማስጠበቅ የሁሉም ኃላፊነት ነው ብለዋል። የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠርም ከሚወሰዱ የጥንቃቄ ተግባራት መካከል ኮንዶም በአግባቡ መጠቀም አንዱ እንደሆነ አብራርተዋል።

ለዚህም ኤ ኤች. ኤፍ ከጤና ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ሀገሪቱ ከሚያስፈልጋት አምስት በመቶውን (አምስት ሚሊዮን) የሚደርሱ ኮንዶሞችን ለመሸፈን እየተሠራ ይገኛል።

በዚህም መሠረት ባለፈው ዓመት ከዋጋ መጨመር ጋር በተያያዘ ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኮንዶም ማስገባት የተቻለ ሲሆን በተያዘው ዓመት ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኮንዶም በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ከማሌዥያ የሚገባ ይሆናል።

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ኮንዶሞች ለኢትዮጵያ ተብለው የሀገሪቱን ደረጃ በጠበቀ መልኩ የተመረቱ ሲሆን ከፍተኛ ተጋላጭነት ላለባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች በነፃ ተደራሽ የሚደረጉ ይሆናል።

ድርጅቱ በ45 ሀገራት የሚንቀሳቀስ ሲሆን ከሁለት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ለሚገኝ ሰዎች ድጋፍ ይሰጣል። ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን በላይ በአፍሪካ ይገኛሉ፤ በኢትዮጵያ ስልሳ ሺ ለሚሆኑ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን ከ100 ሺ በላይ ነፃ የደም ምርመራ እያከናወነ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

# “ሀገርን ማዳን ከልዩነቶቻችን በላይ ስለሆነ ቃታ ከመምዘዝ ይልቅ መነጋገርን እናስቀድም”

## - ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሀገርን ማዳን ከልዩነቶቻችን በላይ ስለሆነ ቃታ ከመምዘዝ ይልቅ መነጋገርን ማስቀደም ይገባል ሲሉ ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ ገለጹ፡፡

ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ የዓድዋ ድል መታሰቢያ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ሀገርን ማዳን ከልዩነቶቻችን በላይ ስለሆነ መጪውን ትውልድ በማሰብ ልዩነትን ለመፍታት ቃታ ከመምዘዝ ይልቅ መነጋገርን ማስቀደም ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ገለጻ፤ የአንድ ሕዝብ ታላቅነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ ታሪክ ሠሪ ሕዝብ መሆን ነው፡፡

“ወንድም በወንድሙ ላይ መነሳት ለማንም ሀገር ኩራት አይደለም፤ አንገት የሚያስደፋ ነው” ያሉት ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ፤ ሁላችንም ልቦና ገዝተን ተነጋግረን ሀገሪቱን ወደ ፊት ማራመድ ይኖርብናል ብለዋል፡፡

ሀገርን ለሆነው ላልሆነው ማናወጥና የሀገርን ዝና ማበላሸት እንደማያስፈልግ ጠቅሰው፤ ለሀገርና ሕዝብ በመቆርቆር፣ በማዘንና በመራራት በአንድነት ሀገርን ለማንሳት የምንጥር ሕዝቦች ልንሆን ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በመካከላችን ለመገንባት የምንሞክረው ግንብ ይቅርና ልዩነቶችን የተሻገረ የዓድዋ ድልን መያዝ አለብን ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ዓድዋ አልበገርም፣ ቅኝ አልገዛም ያለ ሕዝብ ግዙፍ ታሪክ ነው ብለዋል፡፡

ታሪክን መዘከር ብቻ ሳይሆን ከታሪክ መማር እንዳለብን በመግለጽ ዓድዋን የምናወሳው ሀገርን ለማዳን የተሰለፉ ጀግኖችን ለማስታወስና የሚገባቸውን ቦታ ለመስጠት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከታሪክ አንዳንድ ነገሮችን ብቻ መዘን እየተጨቃጨቅን ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ይህ ተግባር የዓድዋ ድል ባለቤት መሆናችንን የሚያጠራጥር ሁኔታ ውስጥ ይከተናል ሲሉ ኮንነዋል።

በዓድዋ ኮረብታዎችና ሜዳዎች ላይ ያለቁት ከሀገራችን አራቱም ማዕዘናት የዘመቱ ዜጎች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በወቅቱ ጀግኖችን ያገናኛቸው የሀገር ፍቅር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የዓድዋ ድል አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት የመጣን ያለአቻ ወራሪ ማሸነፍ የተቻለበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ድሉ የእኛ ብቻ ሳይሆን ቅኝ ግዛትን ይታገሉ የነበሩ ሕዝቦች ድል መሆኑን ተናግረዋል።

በዓድዋ ድል ዘመንም በሕዝቦች መካከል ልዩነቶች እንደነበሩ አስታውሰው፣ ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በመሩት የክተት ጥሪ ሕዝቡ ልዩነቱን ወደ ጎን አድርጎ በመዝመቱ ለድል በቅቷል ብለዋል።

ዓድዋ፣ ሀገር ስትደፈር መላ ኢትዮጵያውያን ከነልዩነታቸው በአንድነት የተነሱበት መሆኑን ጠቅሰው የዓድዋ ድል መታሰቢያም ይህን በተገቢው መልኩ ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ የእኛ ብቻ ሳይሆን ለነፃነት፣ ለሕዝቦች እኩልነት ተስፋን የሰጠ ድል መሆኑን በመግለጽ ዓድዋን የሚያክል ትልቅ የድል ታሪክ ይዘን፣ እስካሁን ታሪካችንን የሚመጥን ሥራ አለመከናወኑ እንደሚያስቆጭ አመላክተዋል፡፡

በመጨረሻም የዓድዋ ድል መታሰቢያ በመዲናዋ እምብርት፣ የዓድዋ ዘማቾች በተነሱበት ቦታ መገንባት መቻሉ ትልቅ ሥራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡






# የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አገኘ

## - አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቶን ጭነት አጓጉዟል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ባለፉት ሰባት ወራት ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘቱን የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር አስታወቀ። አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቶን ገቢና ወጪ ጭነት እንዲሁም ከ115 ሺህ በላይ መንገደኞች ማጓጓዙን ማኅበሩ ጨምሮ ገልጿል፡፡

በማኅበሩ ከፍተኛ የእቅድና የፕሮግራም አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ፍስሐ መብራህቶም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ሰባት ወራት ሁለት ቢሊዮን 256 ሚሊዮን 459 ሺህ ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሰባት ወራት ሁለት ቢሊዮን 158 ሚሊዮን 333 ሺህ ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እንደነበር ያነሱት አቶ ፍስሐ፤ የእቅዱን 104 በመቶ በማሳካት ከሚጠበቀው በላይ ገቢ ማግኘት መቻሉን አስረድተዋል፡፡

አቶ ፍስሐ አክለውም፤ ባለፉት ሰባት ወራት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን ጭነት ለማጓጓዝ ታቅዶ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቶን ጭነት ተጓጉዟል ያሉ ሲሆን፤ የሚፈለገው ያህል ጭነት ያልተጓጓዘው በነበረው የፀጥታና የደህንነት ስጋት እንዲሁም የኮንቴነር ጭነት መጓተት ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ኮንቴነር፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ ተሽከርካሪዎች ስንዴና የምግብ ዘይት በኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አማካኝነት እየተጓጓዘ መሆኑን አቶ ፍስሐ ተናግረዋል፡፡

ድርጅቱ የጭነት ወጪን በመቀነስ ለተለያዩ ተቋማት ውጤታማ አገልግሎት እያቀረበ ነው ያሉት አቶ ፍስሐ፤ የባቡር መስመሩ ኢትዮጵያና ጅቡቲን በማገናኘት ከወደብ ወደ መሐል ሀገር የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦችን በማጓጓዝ ለትራንስፖርት ዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ እያበረከተ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

ድርጅቱ በድሬዳዋ፣ በሞጆ፣ በአዳማ፣ በለቡ፣ በእንዶዴ፣ በዲኬና በመኢሶ እንዲሁም በደወሌ የባቡር ጣቢያ መስመሮች የጭነትና የመንገደኞች የባቡር አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝም ነው አቶ ፍስሐ የገለጹት፡፡

አቶ ፍስሐ እንዳመለከቱት፤ የባቡር መስመሩ በ20 ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በቀጣይም አገልግሎት መስጫ አዳዲስ ጣቢያዎችን ለመክፈት ዝግጅት እየተደረገ ነው።

የባቡር መሠረተ ልማቶች ስርቆት እና የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መዋዠቅ እንዲሁም የፀጥታ ችግር እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ዋና እና ፈታኝ ችግሮች መሆናቸውን አቶ ፍስሐ ተናግረዋል፡፡

# ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያን ቡና በአውሮፓ ገበያ መሸጥ የሚያስችል የውል ስምምነት አደረገ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የኢትዮጵያን ቡና በአውሮፓ ገበያ መሸጥ እንዲችል JDE Pee’t እና Enveritas ከተሰኙ አጋር ድርጅቶች ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡

ሰሞኑን በስካይ ላይት ሆቴል በተደረገው የመግባቢያ ስምምነት ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ(ዶ/ር)፤ ስምምነቱ አውሮፓ ኅብረት በቅርቡ ያወጣውን አዲስ መመሪያ መሠረት ያደረገና የኢትዮጵያ ቡና በአውሮፓ ገበያ ውስጥ በቀላሉ እንዲሸጥ የሚያስችል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአውሮፓ ኅብረት ካለፈው ሰኔ ወር ጀምሮ ቡናን ጨምሮ ሰባት በሚደርሱ የግብርና ምርቶች ላይ አዲስ መመሪያ ማውጣቱን ያስታወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኅብረቱ ባወጣው መመሪያ መሠረት የግብርና ምርቶቹ ከደን ጭፍጨፋ ነጻ በሆነ መንገድ ካልተመረቱ በስተቀር ወደ አውሮፓ ገበያ መግባት እንደማይቻል ነው የገለጹት፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ኅብረቱ ባወጣው አዲስ መመሪያ መሠረት ከዲሴምበር 2020 በኋላ ደን ተጨፍጭፎ ቡና መተከል አለመተከሉን ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ አጋር ድርጅቶቹም ይህን ለማጣራት የገንዘብና ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸው፤ ደን ተጨፍጭፎ የተተከለ ቡና ካለ ወደ አውሮፓ ሀገራት ኤክስፖርት ማድረግ አይቻልም፡፡ ያ ካልሆነና ኢትዮጵያ ከዲሴምበር 2020 በኋላ ደን አለመጨፍጨፏ ከተረጋገጠ ደግሞ የኢትዮጵያ ቡና በቀላሉ ወደ አውሮፓ ገበያ መግባት ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያደረገው ስምምነት ዋናው ዓላማ ኢትዮጵያ በደን ጭፍጨፋ ምን ደረጃ ላይ እንደሆነች መለየት አንዱ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከተጠቀሰው ጊዜ ወዲህ ደን ተጨፍጭፎም ከሆነ መጠኑን በመለየት መልሶ መትከል የሚቻልበት የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ አስቀድሞ ግን የመለየት ሥራው ይሠራል ብለዋል፡፡

በልየታ ወቅትም አውሮፓ ኅብረት ያወጣውን አዲስ መመሪያ የትኞቹ አካባቢዎች ሊያሟሉ እንደሚችሉና የትኞቹ አካባቢዎች እንደማያሟሉ በሳተላይት መረጃ ይሰበሰባል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ JDE Pee’t የተሰኘው አጋር ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣዮቹ ሁለትና ሦስት ወራት ልየታው ተጠናቅቆ ኢትዮጵያ በቡናው ዘርፍ የዕውቅና ሰርተፊኬት ማግኘት እንደምትችልና የኢትዮጵያ ቡና ያለምንም ችግር በአውሮፓ ገበያ መላክ እንደሚቻል ነው ያብራሩት፡፡

የመመሪያው ተግባራዊ መሆን ለኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አንደኛ ገዢ ሀገራት የሚጠይቁትን ዱካውን የተከተለ የቡና ምርት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛ ደን ያልተጨፈጨፈበትን ምርት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ቡና በተሻለ ዋጋ መሸጥና የተሻለ ገቢ ለማግኘት ያስችላል ብለዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ ከአውሮፓ ኅብረት የተለያዩ ድጋፎችን ማግኘት የሚያስችልና ኢትዮጵያ ከኅብረቱ ጋር ያላትን የረጅም ጊዜ የገበያ ግንኙነት እንዳይሻክርና እንዲጠናከር በማድረግ የጎላ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ነው ያሉት፡፡

# “በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ የልማት ግቦችን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለአህጉራዊ ማሻሻያዎች እና አጀንዳዎች ተፈፃሚነት ቁርጠኝነት ሊኖረን ይገባል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በዚህም በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሁሉም አፍሪካውያን በጋራ ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የአጀንዳ 2063 አንዱ ግብ አህጉሪቱን የሠላም ቀጣና ማድረግ ቢሆንም በአህጉሪቱ አንዳንድ ሀገራት በሚፈጠሩ ግጭቶች በርካቶች ለሕልፈትና ለሰብዓዊ ቀውስ እየተዳረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለይ የምሥራቅ አፍሪካ እና የሳሕል ቀጣና የሽብር ስጋት አሁንም ተግዳሮት ሆኖ መቀጠሉን ገልጸው፤ ይህም ከአየር ንብረት መዛባት ችግሮች ጋር ተዳምሮ ለአፍሪካ ፈተና መሆኑን ተናግረዋል።

የሥራ አስፈፃሚው ምክር ቤት ችግሩን በመፍታት ለአጀንዳ 2063 ስኬት የሚበጁ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብ እንደሚጠበቅበትም ተናግረዋል።

አጀንዳ 2063 የአፍሪካ ኅብረትን ማጠናከር ሌላኛው ግብ በመሆኑ ለኅብረቱ ሀብት ማሰባሰብ ፕሮግራም ዳር እንዲደርስ፣ ኢንቨስትመንት እና ፋይናንስ አቅም እንዲጎለብት መምከር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

አፍሪካ በራሷ መቆም የምትችልበትን መሠረት መጣል እና የኅብረቱን ተዓማኒነት ማስጠበቅ እንደሚገባም ገልጸው፤ አፍሪካ ከስትራቴጂክ አጋርነት አኳያ የአፍሪካውያን ድምፅ በዓለም መድረክ እንዲሰማ ጥረቱ ተጠናክሮ ሊቀጥል ሲሉ አውስተዋል።

በአጠቃላይ ሥራ አስፈፃሚ ምክር ቤት በስብሰባው ለውስብስብ አህጉራዊ ጉዳዮች ከዓለም ዓውድ አኳያ የተቃኘ የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ እንዳለበት አመልክተዋል።

የአፍሪካ ኅብረት በርካታ ተቋማዊ ሪፎርሞች ሲያደረግ መቆየቱን አመላክተው፤ በፖለቲካ በኢኮኖሚ አጀንዳዎችም ከዚህ በፊት የነበሩ ሥራዎች አፈፃፀም ሪፖርት ይቀርባል ብለዋል።

በሌላ በኩል ኅብረቱ ከስትራቴጂ አጋርነት አኳያ በተለዋዋጭ ዓለም ጂኦ-ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል።

የፓን አፍሪካ ምክር ቤትን ጨምሮ ተቋማት የኅብረቱን መርሕ በተከተለ መልኩ ሪፎርም፣ እንዲጠናከር የሚያስችል ምክረ ሀሳብ እንደሚጠብቁ አስታውቀዋል።

የኅብረቱ መዋቅር በሰው ኃይልና በመረጃ የዘመነ ይሆን ዘንድ ለተፈፃሚነቱ መትጋት አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

# ኢትዮጵያውያን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚጠቀስ ኅብረብሔራዊ ድል ነው፡፡

የየጁ፣ የወለጋና የሸዋ ፈረሰኞች እንዲሁም የጎንደር፣ የቤኒሻንጉልና የሸዋ ተዋጊዎች አንድም ሳይቀሩ ዓድዋ ላይ ተዋግተው ሲያሸንፉ ያስመሰከሩት ኅብረብሔራዊነታቸውን ነው ያሉት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ዓድዋ ኅብረብሔራዊነት የኢትዮጵያ የወደፊት አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ትምህርት የተሰጠበት ነው፡፡ አጥንታቸው አንድ ላይ ነው የተቀበረው፡፡ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ሆነ ነገ ከኅብረብሔራዊነት ውጪ ሌላ ምርጫ የለንም ብለዋል፡፡

የዓድዋ ጦርነት ከመካሄዱ በፊት አፄ ምኒሊክ በግዛት ማስፋፋት ላይ ተሰማርተው እንደነበርና በዚህም ብዙ ግጭት ውስጥ እንደነበሩ የጠቀሱት ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ፤ ሆኖም ጣሊያኖች ጥቁሮችን የበታች ለማድረግ ይዘው የተነሱትን ርዕዮተ ዓለም ለማስተግበር ኢትዮጵያን በቅኝ አገዛዝ ስር ማድረግ አለብን ብለው ሲንቀሳቀሱ፣ ኢትዮጵያውያን ውስጣዊ ጉዳዮቻቸውን በይደር አቆይተው ኅብረብሔራዊ አንድነትን ፈጥረው ጠላትን ገጥመው ድል ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የክተት አዋጁ በተላለፈ ጊዜ አዝማሪው፣ ፈረሰኛው፣ እግረኛው፣ ስንቅ አቀባዩ፣ ውሃ ቀጂው እና ጠመንጃ ያነገተው ሁሉ ተሰባስቧል፡፡ ኢትዮጵያውያን ጣሊያኖች የነበራቸውን መሣሪያ ታጥቀው ነበር፡፡ በደምብ በመዘጋጀትና በቁጥርም ይበልጣሉ፡፡ በአንድ በኩል ጣሊያን፣ በሌላ በኩል እንግሊዝና ፈረንሳይ ኢትዮጵያን ከበው ነፃነቷን ለመንጠቅ ሞክረዋል፡፡ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የቅኝ ግዛት ወረራውን ለመቋቋም ቢሞክሩም በመጨረሻ በቅኝ ገዢዎች እጅ ወድቀው ሁለተኛ ዜጋ ለመሆን በቅተዋል፡፡ ጣሊያኖች ይህን ታሪክ ኢትዮጵያ ላይ ለመድገም በማንለብኝነት ከፍተኛ ትግል ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም፡፡

ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ድል ያሳዩት ኅብረብሔራዊ አንድነት በድረ ዓድዋም ተከትሎ መሄድ ሲገባው አልሆነም፡፡ ዛሬ ድረስ የእርስ በእርስ ጦርነት እየተከሰተ የሚገኘው ኅብረብሔራዊነትን ባግባቡ በሥራ ላይ ባለማዋላችን ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ታሪክን የግጭት ምንጭ በማድረግ ዘወትር በትናንሽ ነገር ስንፋጭ እንውላለን፡፡ ይህ ነገር መቀየር አለበት ሲሉም ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር) አሳስበዋል፡፡

አክለውም፤ አሁን የሚታየውን መለያየት ለመቀልበስ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመው፣ ፍትሐዊነትን ለማስፈን አንዱ የሌላውን ማንነት ማክበር አለበት ብለዋል፡፡

ዓድዋ ሀገር ወራሪ በኅብረብሔራዊ አንድነት የተሸነፈበትና መልከ ብዙ ሕዝባዊ እሴቶች የታዩበት በመሆኑ ልንጠብቀውና ሀገርን ለማሳደግ ልናውለው የሚገባ አርዓያነት ያለው ታሪካዊ ድል በመሆኑ አፅዕኖት ሊሰጠው እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

# የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን ለመፍታት የተጀመረውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዚህም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተከሰተውን ችግር ተከትሎ የተደረሰውን የፕሪቶሪያ የሠላም ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ከአፍሪካ ኅብረት ጋር በመተባበር እየሠራች መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

አካታች የሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ የሚከሰቱ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት እየተሠራ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በኅብረቱ አባል ሀገራት መካከል የተጀመረውን በመሠረተ ልማት የማስተሳሰር ጥረት እንዲሳካም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህም በቀጣናው ላይ ሠላምን ለማስፈን ለሚደረገው ጥረት አጋዥ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ሀገር መሆኗን ተከትሎ የአፍሪካ ሀገራት ጋር የጋራ ፍላጎቶቻችንን በመጋራት ተግባራዊ ውጤት እንዲገኝ አበክራ ትሠራለች ሲሉም አመላክተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በብሪክስ አባል ሀገራት ኅብረት ውስጥ በንቃት መሳተፍ ደግሞ የደቡብ ለደቡብ ግንኙነትን እውን ለማድረግ ያስችለናል ነው ያሉት፡፡

አፍሪካ ለኢኮኖሚ ብልጽግናዋ የሚረዳት እምቅ የኢኮኖሚ አቅም ያላት ሲሆን፤ አጀንዳ 2063 ደግሞ የሁላችንም የኢኮኖሚ መዳረሻ ግብ ማረፊያ ነው ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ በአባል ሀገራት መካከል የሚደረገው ውጤታማ ትብብር ለዚህ መሳካት የማይተካ ሚና አለው ብለዋል።

የአፍሪካ ነፃ ገበያን እውን በማድረግ በሀገራቱ መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ እውን ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች መጠናከር እንዳለባቸው አንስተው በዚህ ረገድ ለቀጣናው እውን መሆን የራሷን ሚና እየተጫወተች መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የአፍሪካ ቋንቋዎችን ለማበልጸግ የተያዘውን ግብ መሠረት በማድረግ ለአህጉራችን ዕድገት የራስን አበርክቶ



ለመጨመር በማሰብ አማርኛ የአፍሪካ ኅብረት የሥራ ቋንቋ እንዲሆንም ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

ለዚህ ደግሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መተዳደሪያ በይፋ ከተፈረመባቸው አራት ቋንቋዎች አንዱ አማርኛ መሆኑን መገንዘብ ጥያቄው አግባብ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋን በኅብረቱ የሥራ ቋንቋነት መቀበል የቋንቋ ስብጥሩን ከማስፋት ባለፈ እንደ አፍሪካዊ ያለንን የጋራ ማንነት የሚያረጋግጥ ይሆናልም ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ለሁሉም ተደራሽ የሆነ የማይበገር የትምህርት ሥርዓት ለመዘርጋት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ቅድሚያ በመስጠት እየሠራች ነው።

በሀገር አቀፍ የትምህርት ምገባ ፕሮግራማችን ከስድስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን በየዕለቱ በመመገብ ለትምህርት ያለውን አዎንታዊ ሚና በተግባር እያረጋገጠች መሆኑንም አምባሳደሩ ጠቅሰዋል።

መንግሥት የትምህርት ሥርዓቱን በጥራት የታገዘ ለማድረግ አቅዶ በወሰዳቸው እርምጃዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች አዳሪ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት የትምህርት ተደራሽነትንና ጥራት ለማረጋገጥ እየተሠራ ይገኛልም ነው ያሉት።

የአህጉሪቱን የትምህርት ጥራት እውን ለማድረግ አባል ሀገራቱ በትብብር መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመው ከቡድን 20 አባል ሀገራት ጋር በመጣመር መሥራትም እጅጉን አስፈላጊ ነው ብለዋል።

37ኛው የኅብረቱ ጉባኤ “ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን አፍሪካዊ ማስተማር፤ የማይበገሩ የትምህርት ሥርዓቶች በመገንባት በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ፣ የሕይወት ዘመን፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት“ በሚል መሪ ሃሳብ ይካሄዳል።

# የሐሮማያ ሐይቅ ተስፋና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

2012 ዓ.ም ኃይለኛ ዝናብ በመዝነቡ ሐይቁ ተመልሶ እንደመጣ የሚያስታውሰው አቶ ረመዳን፤ በአሁኑ ጊዜም 360 ወጣቶች ተደራጅተው ሐይቁን በማስጎብኘትና ዓሳ በማጥመድ ሥራ ላይ ተሠማርተው እንደሚገኙ ነግሮናል። ሐይቁ በመመለሱ ደስተኞች ነን። እኛም ሆነ ልጆቻችን ከ17 ዓመታት በኋላ ወደ ቀድሞ ሥራችን ተመልሰናል ነው ያለው።

“ሐሮማያ ሐይቅ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ብቸኛው ሐይቅ ነው።ለ17 ዓመታት ደርቆ በመቆየቱ የኳስ ሜዳና የከብቶች ግጦሽ ቦታ ሆኖ ቆይቷል” የሚለው በሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የሐሮማያ ሐይቅ ተፋሰስ ልማት የፕሮጀክት አስተባባሪና ተመራማሪ ዲኔ ረሺድ፤ የሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የሐሮማያ ሐይቅ መድረቅን ተከትሎ ዳግም ሐይቁ እንዲመለስ የተቀናጀ የሐሮማያ ሐይቅ የተፋሰስ ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ሥራ ከገባ 10 ዓመታትን አስቆጥሯል ብሏል። ፕሮጀክቱ የተራቆቱ አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ይገልጻል።

በበጋ ወቅት እርከኖችንና የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን ይሠራል። በክረምት ደግሞ የተለያዩ ችግኞችን እየተከለ ይገኛል። ይህን ተከትሎ በ2012 ዓ.ም በክረምት ወቅት ከፍተኛ ዝናብ በመዝነቡ ለ17 ዓመታት ደርቆ የነበረው የሐሮማያ ሐይቅ ዳግም ሊመለስ ችሏል ሲል ያስረዳል።

ሐይቁ ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታትም በተካሄዱ ጥናታዊ የልኬት ሥራዎች የውሃ መጠኑ ጭማሪ ማሳየቱን ነው የገለጸው። በመጀመሪያው ዓመት ልኬት የሐይቁ የውሃ መጠን 8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ተመዝግቧል። በሁለተኛው ዓመት 8 ነጥብ 64 ሚሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ጭማሪ ሲያሳይ ዓምና ደግሞ ወደ 8 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኪዩብክ ሜትር ከፍ ሊል ችሏል። ዘንድሮ ደግሞ ውጤቱ ሲታወቅ ይፋ እንደሚሆን ተመራማሪው አብራርተዋል።

የሐይቁ ጥልቀት በአማካይ አራት ሜትር መሆኑን ገልጾ፤ 226 ሄክታር ስፋት እንዳለው ጠቅሷል። አሁንም የሐይቁን ሕልውና ለማስጠበቅ በአካባቢው የሚገኙ ተራራዎችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ የአፈርና ውሃ ጥበቃና የእርከን ሥራ እንደሚሠራ የሚናገሩት አስተባባሪው፤ በክረምት ችግኞች ይተከላሉ። ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በመተባበር በዓመት ሁለት ጊዜ የጽዳት ዘመቻ ይደረጋል ነው ያሉት።

እነዚህ ሥራዎችን ለማከናወንም በዓመት ስምንት ሚሊዮን ብር ያህል ወጪ እንደሚያደርግም ገልጸዋል። በአሁኑ ጊዜም ዩኒቨርስቲው የሐይቁን ሕልውና ለማስቀጠል ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል።

በሐይቁ ዙሪያም ወጣቶች ተደራጅተው ጎብኚዎችን የጀልባ አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ ሐይቁን ለመጎብኘትም በዓመት እስከ 50ሺህ ጎብኚዎች እንደሚመጡ አመልክተዋል።

የዘንድሮን የውሃ ልኬት ሳይጨምር ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት የሐይቁ የውሃ መጠን እየተሻሻለ መጥቷል የሚሉት ደግሞ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ አስተዳደር የውሃ መረጃ አያያዝ ከፍተኛ ባለሙያ ብርሃኑ ለገሠ ናቸው።

እሳቸው እንደሚሉት፤ አሁንም የሐይቁ ሕልውና፣ ንጽሕናና መጠን ተጠብቆ ለቀጣዩ እንዲተላለፍ ብዙ ሥራዎች ይጠብቁናል። እነዚህን ከሠራን የሐይቁን ሕልውና ማረጋገጥ ሲቻል በአንጻሩ ቀጣይነት ያላቸው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ካልተሠሩ፣ በሐይቁ ዳርቻ ላይ ያሉ እርሻዎች የሚስፋፉናና ጥንቃቄ የጎደላቸው ከሆኑ የሐይቁ ሕልውና ስጋት ላይ መውደቁ አይቀርም ነው ያሉት።

የተማከለ የውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈን ሲቻል፣ የተጀመሩት የውሃና የአፈር ጥበቃዎች፣ የችግኝ ተከላዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ከሆነ ሐይቁ የውሃ መጠን እያጨመረና አስተማማኝነቱ እየተረጋገጠ ይሄዳል ሲሉ ምክረ ሀሳብ አቅርበዋል።

በሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የውሃ ምሕንድስና ተመራማሪ ነጋሽ ተሰማ በበኩላቸው ባለፉት አራት ዓመታት የሐሮማያ ሐይቅን የውሃ መጠን ስንለካና ስናጠና ቆይተናል። ይህ ጥናት እንደሚያሳየው ባለፉት አራት ዓመታት ሐይቁ አስተማማኝ ደረጃ ነው ለማለት ይከብዳል። ምክንያቱም የሐይቁ ሕልውና ቀጣይነት ለማረጋገጥ አሁንም ብዙ ሥራዎች መሥራት አለባቸው ይላሉ።

በመጪዎቹ ተከታታይ ዓመታት የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎች ካልተሠሩ ሐይቁ አሁንም ስጋት ላይ ነው የሚሉት አቶ ነጋሽ፤ አንደኛ በየቀኑ ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ውሃውን በውሃ መሳቢያ ሞተር እየሳቡ እርሻቸውን ውሃ ያጠጣሉ። ይህ ሁሌም በዚህ መልኩ የሚቀጥል ከሆነ የሐይቁ የውሃ መጠን እየቀነሰ መሄዱ አይቀርም። እንዲሁም በሐይቁ ዳርቻዎች ያሉ እርሻዎች ከፍተኛ ዝናብ ሲዘንብ አፈሩ እየተሸረሸረ ወደ ሐይቁ ይገባል። ይህም ሐይቁ በደለል እንዲሞላ ያደርጋል። ስለዚህ እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ኅብረተሰቡን ያሳተፈ የተጠናከረና የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መሥራት ግዴታ መሆኑን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከመሪዎቹ ስብሰባ አፍሪካውያን ብዙ ይጠብቃሉ!

አፍሪካውያን በቀደሙት ዘመናት የተሞኙትን የተሟላ ነፃነት እውን በማድረግ ነገዎቻቸውን ብሩህ ለማድረግ ከነፃነት ትግሉ ያልተናነሰ የትግል ቁርጠኝነትና መስዋዕትነት እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል። ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርም አሁን ያለው አፍሪካዊ ትውልድ ዋነኛ ኃላፊነት ነው።

አፍሪካውያን አባቶቻችን በቀደመው ዘመን የተጫናቸውን የቅኝ ግዛት ቀንበር፤ ከላያቸው ላይ ለመጣል እዚህ እዚያም የጀመሩት የእምቢተኝነት ንቅናቄ የትግል ዘር እየሆነ፤ በብዙ መስዋዕትነት ነፃነታቸውን በደማቸው መቀዳጀት ችለዋል። ነፃነት ምን ያህል ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችልም ለመጪዎቹ ትውልዶች ተጨባጭ ተሞክሮዎችን ጥለው አልፈዋል ።

በአንድ በኩል ለነፃነታቸው መሠረት የሆነውን አንድነታቸውን ማጽናት እንዳይችሉ የሚፈጠሩ የልዩነት ትርክቶችንና ሴራዎችን መቋቋም የሚያስችሉ እልህ አስጨራሽ ሥራዎችን እየሠሩ፤ በሌላ በኩል ትግሉ በራሱ የፈጠረውን የእምቢተኝነት ግለት እንዳይቀዛቀዝ የአስተሳሰብ መሠረት እንዲኖረው ብዙ ርቀት ተጉዘዋል።

ኢትዮጵያኒዝምን ጨምሮ የፓን አፍሪካኒዝምን እሳቤ፤ የትግል ርዕዮተ ዓለም አድርጎ በመውሰድ፤ የነፃነት ትግሉ የቅኝ ግዛትን ቀንበር ከመስበር ባለፈ አፍሪካዊ የተስፋ ራዕይ እንዲኖረው፤ የትግሉ ስኬት መለኪያም የአህጉሪቱን ሕዝቦች የተሟላ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ነፃነትን ታሳቢ ያደረገ ሆኗል ።

በዚህም ትግሉ በአንድ ወቅትና በአንድ ትውልድ ተጀምሮ የሚያበቃ ሳይሆን በትውልዶች ቅብብሎሽ የሚከወን፤ ለስኬታማነቱም የእያንዳንዱን ትውልድ የነቃ ተሳትፎ፤ ከፍ ያለ ቁርጠኝነት ከሁሉም በላይ ደግሞ የአፍሪካውያኑን መስከንና መደማመጥ የሚጠይቅ ሆኗል ።

የትናንቱ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ትግላቸው ስኬት ከሁሉም በላይ አንድነታቸው የፈጠረው አቅም መሆኑን በአግባቡ በመረዳት፤ ይህን አቅማቸውን ማጠናከር፤ ልዩነቶቻቸውን ከማጥበብ ጀምሮ ልዩነት ፈጣሪ ሴራዎችን እና ትርክቶችን መታገል ለነገ ድላቸው ዋነኛ መሠረት ነው ።

ይህንን እውነታ በአግባቡ በመረዳት፤ ለአፍሪካውያን የተሟላ ነፃነት ለማቀናጀት ትናንት በብዙ መስዋዕትነት የተጀመረው ትግል የሚጨበጥ ፍሬ እንዲያፈራ አሁን ላይ ያሉ የአህጉሪቱ መሪዎች ኃላፊነት ከትናንቱ አፍሪካውያን የነፃነት ታጋዮች የበለጠ እንጂ ያነሰ እንደማይሆን ይታመናል ።

የአሁኑ ትግል የተሟላ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ነፃነትን በመቀዳጀት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን የሚያጎናጽፍ ከመሆኑ አንጻር፤ አሁን ባለው ተለዋዋጭ፣ ውስብስብ እና በብዙ ፍላጎቶች የተሞላ ዓለም ውስጥ በቀላሉ ማሳካት የሚቻል አይሆንም። በብዙ መስከን መደማመጥን የሚፈልግ ነው ።

አጠቃላይ የሆነው የአህጉሪቱን ሕዝቦች የቀደመ ትግል፣ ትግሉ የፈጠረውን መነቃቃት፣ መነቃቃቱ የፈጠረውን መሻት፣ መሻቱን ተጨባጭ ለማድረግ የተቀመጡ የትግል መርሆዎችን በአግባቡ ማስተዋል፣ ክፍተታቸውን መገምገምና ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ ማጥበብ ያስፈልጋል ።

በተለይም የአህጉሪቱ መሪዎች የአህጉሪቱን ሕዝቦች በማስተባበር፣ ከተባበረው ማንነታቸው የሚፈጠረውን አቅም በማቀናጀት፣ በቀደመው ዘመን በብዙ መስዋዕትነት አንድ ምዕራፍ መጓዝ የቻለውን የአህጉሪቱን ሕዝቦች ራስን የመሆን ትግል ተጨማሪ ርምጃ እንዲራመዱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህም በየትኛውም ሁኔታና መንገድ የሚያደርጓቸው መሰባሰቦች፣ አፍሪካውያኑን ዛሬ ላይ ካሉባቸው ተደራራቢ ችግሮች መታደግ የሚያስችሉ፣ የራሳቸውን ብሩህ ነገዎች ተጨባጭ በማድረግ የታሪክ ሂደት ውስጥ ተጠቃሽ ሊያደርጓቸው የተገቡ ሊሆኑ ይገባል። መሰባሰባቸውም ይህን ታሳቢ ማድረግም ይኖርበታል።

በዚህ ሳምንት ማብቂያ ላይ የሚደረገው የአህጉሪቱ የመሪዎች ስብሰባ ከዚህ አኳያ ብዙ የሚጠበቅበት ነው። በተለይም የአህጉሪቱን ሕዝቦች ካሉባቸው ውስብስብ ችግሮች ወጥተው፣ ብሩህ ነገዎቻቸውን እውን ለማድረግ ከሁሉም በላይ በአንድነት መቆማቸው ወሳኝ ስለመሆኑ አፅንዖት ሰጥቶ እንደሚነጋገር ይጠበቃል።

አፍሪካውያን ያላቸውን የተፈጥሮ ፀጋዎች አቀናጅተው፣ በተናጠል ሊገፉት የማይችሉትን ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖ መሻገር እንዲችሉ፣ የኢትዮጵያን አዲስ የትብብር እሳቤ እንደ አንድ ማሳያ በመውሰድ፣ እሳቤውን የሚያበረታቱበት አጋጣሚ እንደሚሆንም ይታመናል።

ይህ እሳቤ ከፓን አፍሪካኒዝም የተቀዳ፣ የአፍሪካን ወንድማማች ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት ማስፈን የሚያስችል፣ እስከ ዛሬ በተናጠል ሲታገሉት የነበረውን፣ አቅማቸውን ሲከፋፍል የኖረውን፣ የጠባቂነት መንፈስ በማስወገድ፣ ሁለንተናዊ አህጉራዊ አቅም መገንባት የሚያስችል፤ ዓለም አቀፍ ተደማጭነትን የሚያሳድግ ጭምር ነው!

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ
ኢፕድ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለአፍሪካውያን ብሩህ ነገዎች ከመሪዎቿ ብዙ ይጠበቃል

እፀገነት አክሊሉ

በሀገራችን በ1955 ዓ.ም አንድ ኩነት ሆነ። ይህ ኩነት ማንም ይሆናል ብሎ ያላሰበው ከመሆኑም በላይ አስደናቂም አስደማሚም ነበር። ወቅቱ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት እሳት ውስጥ የነበሩበት፤ አፍሪካዊ እንደ ሙሉ ሰው ተቆጥሮ ሃሳቡ ተደምጦ ጥያቄውና ፍላጎቱ ታይቶ ይሁንለት፤ ይደረግለት የሚባልለት ወቅት አልነበረም።

ከዛ ይልቅ አፍሪካውያን ተፈጥሮ ያደለቻቸውን የተፈጥሮ ሀብት ቦጥቡጦ ለመበልጸግ፤ ዜጎችንም ባሪያ አድርጎ መግዛት የብዙዎቹ ምዕራባውያን ሃሳብና ዓላማ ብሎም ተግባር ነበር።

በዚህ መካከል ግን ትልቅ ሀሳብን ያነገበችው ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ቀንበርን አልሸከምም እኔ ከማንም አላንስም በሀብትና በንብረቴ የማዘው ራሴ ነኝ ዜጎቼም በባርነት የሚማቀቁበት አንዳችም ምክንያት የለም ስትል በዓለም አደባባይ ላይ ወጣች። ይህ ለብዙዎች ትንግርት ቢመስልም ሆኖና ተችሎ የተመለከቱት ሐቅ ሆነባቸው።

ይህች ተምሳሌት የሆነች ሀገር በጠንካራ መሪዋ አማካኝነት በዓለም አደባባይ ስሟን የሚያስጠራ ቀና የሚያደርጋት መሰሎቿንም ቀና የሚያደርግና ካሉባቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች መንጥቆ የሚያወጣ ሃሳብ ይዛ ብቅ አለች። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታን።

የዛሬ 61 ዓመት እነ ኬንያታ፣ ኃይለሥላሴ፣ ንክሩማ፣ ኔሬሬ እና ገማል አብዱል ናስር የተባበረችዋን አፍሪካ ለመመሥረት የመሠረት ድንጋይ አኖሩ! የተባበረች አፍሪካ፣ ከቅኝ ግዛት ነፃ የወጣች አፍሪካ ፣ የበለፀገች አፍሪካ አልመው ፣ ይኸው ስድስት አስርተ ዓመታትን አስቆጠሩ።

በእርግጥ አንድነቱ ወደ ኅብረት ይደግ እንጂ ዛሬም ድረስ የተመሠረተበትን ዓላማ ከግብ አድርሷል ለማለት የማያስደፍሩ ብዙ ምክንያቶች አሉ። አፍሪካ ኅብረት ሲመሠረት የቆመለት የነፃነት የሉዓላዊነት ከድህነትና የመውጣት ሕልም ብዙም እልፍ ሲል አልታየም።

አፍሪካና አፍሪካውያን ዛሬም የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ናቸው። አፍሪካውያን ዛሬም ከእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ተላቀዋል ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚያበቃ ሁኔታ አይታይም።

አፍሪካውያን ዛሬም ከስደትና የነጮቹን ደጃፍ ከመርገጥ አልወጡም። ለምን ቢባል እንደ ስሙ ኅብረት በማጣታችን ነው። ሲቋቋም እንደነበረው አፍሪካውያን ተረዳድተንና ተፋቅረን እንደ አንድ ሆነን መቆም ስላቃታቸው ነው።

**አፍሪካውያን ዛሬም ከስደትና የነጮቹን ደጃፍ ከመርገጥ አልወጡም። ለምን ቢባል እንደ ስሙ ኅብረት በማጣታችን ነው። ሲቋቋም እንደነበረው አፍሪካውያን ተረዳድተንና ተፋቅረን እንደ አንድ ሆነን መቆም ስላቃታቸው ነው**

በእኔ አረዳድ እነ አፄ ኃይለሥላሴና ሌሎቹም ጠንካራ አፍሪካውያን መሪዎች ያቆዩትን የትብብርና የአንድነት ስሜት ይዘን ቀጥለናል ለማለት አልደፍርም። እንደ ቀደሙት አባቶቻችን ሀሞተ ኮስታራ ሆነን ለነጮች የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት እምቢ አልገዛም ማለት ተስኖናል ።

ዛሬም ግን አፍሪካን የአፍሪካውያን የማድረጉ እድል ሙሉ በሙሉ ከእጃችን ወጥቷል ለማለት አይቻልም። ዛሬም ቢሆን ሀብታችንን በሚገባ አልምተን፣ ከእርስ በእርስ ፍጅት "ከመፈንቀለ መንግሥት፣ ከመፈናቀልና ከማፈናቀል፣ ከኅታች አስተሳሰብ ወጥተን ችግሮቻችንን ልዩነቶቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ የምንፈታ ስልጡን ሕዝቦች መሆን ከቻልን ጊዜው አለን።

ለዚህ እነሱ (ምዕራባውያኑ) እንደሚሉን ችግረኛ ደሃ ሳንሆን ተፈጥሮ ለእነሱ ያላደለቻቸውን በረከቶች ሁሉ የተሰጠችን የተመረጥን ድንቅ ሕዝቦች መሆናችንን መጀመሪያ ማመን ይገባናል፤ ከዛም ሀብታችንን እንዴት ነው መጠቀም ያለብን የሚለውን ደግሞ ሰከን ብሎ ማሰብ ይጠይቃል ።

ከሁሉ በላይ አስቸጋሪው ሀብት ሳይሆን የሀብት ፍትሐዊ ክፍፍል ነውና፤ እንዴት ነው በፍትሐዊነት ለሁሉም የሚዳረሰው፤ በምን መልኩ ነው የሥራ እድል የሚፈጠረው፤ እንዴት ባለው መንገድ ነው የዘመኑ ቴክኖሎጂዎችን አፍልቀን ኑሯችንን ፤ ሕይወታችንን የምናቀለው፤ በምን መልኩ ነው በየጊዜው ፈልገንም ሳንፈልግም ከሚመጣብን ጦርነትን ከምናባክነው ሀብት የምንድነው? በቀናነት መጠየቅ፤ ለተግባራዊነቱም መጣር ይገባናል።

የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በየዓመቱ ይደረጋል ይህ ምንልባትም ለእኛ ለኅብረቱ መሥራቾች በጣም ትልቅ ነገር ነው፤ ምክንያቱ ደግሞ የኅብረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ መሆኑ የሚያማቸው ብዙ ጠላቶች ስላሉን። ግን ደግሞ እነዚህ መሪዎች በዓመት ለአንድ ጊዜ ተገናኝተው ምን አድርገው ነው ወደመጡበት መመለስ ያለባቸው? የሚለው እንደ አፍሪካዊ ሊያሳስበን ይገባል።

በተለይም አሁን በደረሰንበት ጊዜ እነዚህ መሪዎች በአንድ ላይ ቁጭ ብለው ሊወያዩባቸው፤ ሊፈቷቸው አቅጣጫ ሊያስቀምጡባቸው የሚገቡ በርካታ የቤት ሥራዎች ያሉበት ጊዜ ነው። አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት በእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ናቸው፤ ሕዝቡም ስደትን እንደ አማራጭ አይቶ በዓለም ላይ እየተሰደደ ግማሹም ባሕር ለማቋረጥ በሚያደርገው ጥረት እዛው እየሰመጠ የአውሬ እራት እየሆነ ነው። በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ራሳቸውን አግዝፈው ከሚባለው በላይ ሀብት ሰብስበው ጆሯቸውንም አይናቸውንም ደፍነው የታዩ አፍሪካውያን መሪዎች አሉ።

የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ የእርስ በእርስ እልቂት እና ፍጅት የሚያበቃበትን፤ አህጉራችን ለዜጎቿ የመከራ ዋሻ ከመሆን ወጥታ ያላትን ሀብት ተጠቅማ ካለችበት ድህነትና ኋላቀርነት የምትወጣበት፤ ከተናጠል የልማት ጉዞ ወጥታ የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ መንገድ መጓዝ የምትችልበትም መልካም አጋጣሚ መፍጠር የሚችል ቢሆን እመኛለሁ ።

አበው ሲተርቱ "ሸክላ ሰሪ በገል ትበላለች" ይላሉ ይህ አባባል ትልቅ ነው በተለይም ለእኛ አፍሪካውያን፤ ምክንያቱ ደግሞ ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን ሆኖ ተስማምተን ተደማምጠን ተፋቅረን መጠቀም ስላቃተን ብቻ ሌሎች በሀብታችን እየበለጸጉ እኛ ሁሌም "በገል" መብላታችንን ያሳያል። ይህ ሁኔታ ሊቀየር፤ ሊቀየርም ብቻ ሳይሆን እንደ አፍሪካ አንድ ሆነን በኅብረት ቆመን ተባብረንና በልጽገን የምንታይበት ጊዜ ሊቃረብ ይገባል።

አፍሪካውያን "እንኳን ደህና መጣችሁ"! መምጣታችሁ አስደሳች ነው። ነገር ግን መምጣታችሁን መሰብሰባችሁን በፍሬያማ ንግግሮች ውሳኔዎች በጠንካራ አቋሞች አስደግፋችሁ እንደ እነ ቀደሙት የኅብረቱ መሥራቾች በአንድነት የሚዘከር፣ የሚነገርና የሚወደስ ለትውልድ የሚቆይ ታሪክ ጻሐፊ ያድርጋችሁ። አበቃሁ!

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የፓን አፍሪካኒዝም ጥንስስ እና የኅብረቱ ግብ፤

እንደ አውሮፓውያኑ የጊዜ ቀመር በ1812 በምዕራብ ቨርጂኒያ ግዛት ቻርለስ እንደተወለደ ታሪክ የሚያወሳን ማርቲን ሮቢን ሰን ዴላኒ፤ አባቱ በቅኝ አገዛዝ ዘመን ከአፍሪካ አኅጉር በባርነት የተወሰደ ነው፤ የግለሰቡ ልዩ መታወሻው ጥቁር አሜሪካዊያን ወደ አኅጉራቸው አፍሪካ እንዲመለሱ የሚያበረታታ ንቅናቄን ማስጀመሩ ነው፤ በአሜሪካን ወታደራዊ ተቋም ውስጥ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካ አሜሪካዊ ሹም የነበረው ዴላኒ፤ በዘመኑ የነበረው የባርነት ቀንበር እና የጥቁር የበታችነት አሳሳቢ እና ተሰፋ የሚያስቆርጥ ስለመሆኑ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ደጋግሞ ያነሳም ነበር። አቋሙ ይህን ያህል ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆን ያስቻለው ቤተሰቦቹ ለልጃቸው ከቆዳ ቀለም ማንነታቸው ያለፈ ሐሳብ እና ማንነት እንዲይዝ አድርገው ማሳደጋቸው ነው።

ከ200 ዓመታት በፊት ወደዚህች ምድር የመጣው ማርቲን ዴላኒ የባሪያ ንግድን የሚቃወም፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች፣ የሕክምና ባለሙያ፣ ወታደር፣ ጋዜጠኛ እና የጥቁር ነፃነት አቀንቃኝ ነበረ ይለናል ከማኅበራዊ ድረ ገጽ ያገኘሁት መረጃ። ማርቲን በበርካታ የጥቁር ነፃነት ንቅናቄዎች ላይ ተሳታፊ፤ በአሜሪካ ውስጥ በየሳምንቱ ይታተም በነበረው ዘ ሚኒስትሪ ጋዜጣ ላይ ያለ ማቋረጥ የጻፈ፤ ከኒውዮርኩ የጥቁር መብት ተሟጋች ፍሬድሪክ ዳግላስ ጋር ዘ ኖርዝ ስታር በሚል በበርካቶች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፈ ስለ ጥቁሮች ነጻነት እና እኩልነት የሚሞግት ጋዜጣ በማሳተም ፋና ወጊ የነበረ፤ ጥረታቸው ቀጥሎ ከ1865 እስከ 1872 የጥቁር አፍሪካ አሜሪካውያን የነፃነት ቢሮ Freedmen's Bureau በመምራት ከ4 ሚሊዮን የሚበልጡ ጥቁር አሜሪካውያን ከባርነት ነፃ እንዲወጡ አድርገዋል።

ልክ እንደ ማርቲን ሁሉ ዛሬ ለበርካታ አፍሪካውያን ቀና ብሎ መራመድና ለጥቁሮች እኩልነት በታገለ የፓን አፍሪካኒዝም ፅንሰ ሐሳብ አራማጅ በመሆን የአሌክሳንደር ኩርሜል ስም ይነሳል። በ1819 በኒውዮርክ የተወለደው አሌክሳንደር ኩርሜል በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ትምህርቱን ያጠናቀቀ ሲሆን፤ በ1853 ወደ ሊቢያ በመሄድ የሰው ልጅን እኩልነት እና የጥቁሮችን ነፃነት የሰበከ የፓን አፍሪካ ንቅናቄ መስራች እና አራማጅ ነበር። ለ20 ዓመታት በሊቢያ በቆየበት ወቅት አሌክሳንደር አፍሪካውያን አንድ ሐሳብን በማንገብ ለነፃነታቸው እንዲቆሙ ሰርቷል። አፍሪካውያን ለአፍሪካ የሚል ፅንሰ ሐሳብ በማራመድም እሱን ተከተው ለንቅናቄው ፈርጥ ለሆኑት እነ ማርከስ ጋርቬይ፤ ፓወል ላውረንስ ዱንባል እና ዱ ቦንሲ መንገድ ከፍቷል።

እንዲህ እያለ የተቀጣጠለው የጥቁሮች የነፃነት ማዕበል እየላቀ ሄዶ በ1980 የጥቁሮች ትግል የብሔርተኝነት (ናሽናሊዝምን) አስተሳሰብ እና መርህ ይዞ ንቅናቄው ዓለም አቀፋዊ እንዲሆን ተደረገ። አዲሱ የብሔርተኝነት አስተሳሰብ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ኅብረት እንዲሁም ራሱን ከአውሮፓ ኅብረት ያገለለው የአውሮፓ ፖለቲካል ዶክትሪን እንዲመሰረት ምክንያት ሆኗል። የኋላ ኋላም በ1920 በዓለም ላይ ሰላምን ለማስፈን እና አገራት የእርስ በእርስ ጦርነትን ለማራቅ በፓሪስ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ መቋቋም ምክንያት ሆኗል።

አፍሪካውያን ለነፃነታቸው በታገሉባቸው ዓመታት ውስጥ አንድነታቸውን ለማጠናከር ፓን አፍሪካኒዝም የላቀ አስተዋፅኦ እንደነበረው፤ ንቅናቄውን የጀመሩት የመጀመሪያዎቹም ቢሆኑ አፍሪካ አንድ ሆና ማየትን ከመሻት በመነጨው ሕልማቸው ውስጥ ከባርነት እና ቀኝ ግዛት ነፃ ከመውጣት ባሻገር ተያይዞ ማደግን እና ከድህነት አዘቅት ውስጥ መውጣትን አልመው ታግለዋል። ፓን አፍሪካኒዝም አፍሪካውያን እንዲሁም ከአፍሪካ የተሰደዱ ሁሉ ተመሳሳይ ፍላጎት አላቸውና አንድ ሊሆኑ ይገባል የሚልን ሐሳብ ያራምዳል።

ፓን አፍሪካኒዝም ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴን፣ ዩዌሪ ሞሶቬኒ፣ ኩዋሜ ንክሩማህን፣ ሞአመር ጋዳፊን ብሎም ቶማስ ሳንካራን እና ሌሎች ለአፍሪካ አንድነት የቆሙ አፍሪካውያንን አፍርቷል። እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ሐምሌ 9/2002 በደርባን ደቡብ አፍሪካ የአፍሪካ ኅብረት ሲመሰረት ይህንን የአንድነት ስሜት አንግቦ ነው። አፍሪካ ለአፍሪካውያን ትሆን ዘንድ አፍሪካውያን ደግሞ ባላቸው እና በሚኖራቸው ሁሉ ለአፍሪካ እንዲቆሙ በመጠየቅ የፓን አፍሪካኒዝም ፅንሰ ሐሳብ ዛሬም እንዲዳብር ሆኗል። በአፍሪካ ኅብረት በርካታ ሐሳቦች ይስተናገዳሉ።

ለአፍሪካ እና አፍሪካውያን የሚበጁ ቴክኖሎጂ፣ የባሕል እና የሳይንስ የልህቀት ትስስሮች ይመሰረታሉ። በ2024 ከጦርነት እና ሰላም እጦት ነፃ ለመሆን፣ ከርሃብ እና ኋላ ቀርነት ለመላቀቅ እምርታዊ ለውጥ የምታስመዘግብ፤ በአዲስ አስተሳሰብ አዳዲስ ግቦችን የተለመች አፍሪካን ለመገንባት መሪዎቿ በኅብረቱ መዲና አዲስ አበባ ጉባኤያቸውን ያደርጋሉ። በዚህ ስብሰባቸው አለፍ ሲልም በአጀንዳ 2063 የተያዙ ግቦችን ገቢራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ፍኖተ ካርታዎች ገቢራዊነታቸው እንዴት እየሄደ ነው የሚለው እየተመዘነ አቅጣጫዎች ይቀመጣሉ።

ጋዜጠኛ ኤልያስ መሠረት በበኩሉ፤ ትውልደ-አፍሪካውያን የጋራ ጥቅም፣ እጣ ፈንታ እና ታሪክ ባለቤት መሆንን የሚገልፅ ሲሆን ለዚህም ትብብርን እና በጋራ መስራትን ያበረታታል። ታዲያ በዚህ ሀሳብ ዙርያ በቀደመው ግዜ ታላላቅ ገድሎች የተፈፀሙ ቢሆንም አሁን፣ አሁን ግን ስም ብቻ እየሆነ እንደመጣ በርካታ የአፍሪካ ፀሀፊያን ያነሳሉ። እነ ስቲቭ ቢኮ፣ ጁሊየስ ኔሬሬ እና ማርከስ ጋርቬይ ያነገቡት እና ብዙ መስዋዕት የከፈሉለት መርህ የት ደረሰ ብለው የሚጠይቁ በርካቶች ናቸው። ከቅርብ ግዜያት ወዲህ ግን አፍሪካውያን ከውጭ ሀገራት ይደርስብናል ያሉትን ጫና እና ጣልቃ ገብነት ለመከላከል የፓን አፍሪካኒዝም መርህን ደጋግመው ሲያነሱ ተስተውሏል፣ የአፍሪካ ሀገራትም በመርሁ ዙሪያ ሲተባበሩ ተስተውሏል። እርግጥ ነው አንዳንድ ታዛቢዎች ይህ "የመንግስታት መደጋገፍ ብቻ" እንደሆነ ጠቅሰው "ነግ በኔ" በሚል እሳቤ እንደሚመራ ለማስረዳት ይሞክራሉ።

ኢትዮጵያ በቀደሙት ዓመታት ፓን አፍሪካኒዝምን ካራመዱ እና ከፍ ካደረጉ ሀገራት መሀል አንዷ ነበረች፣ ለዚህም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የነበራቸው ድርሻ እጅግ የጎላ ነበር። በቅርብ ዓመታት ግን ይህ መርህ በአብዛኛው ተረስቶ ነበር፣ ለዛም ይመስላል ብዙ ትኩረት ተሰጥቶት የማያውቀው። ሌላው ቀርቶ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት እንደሚደረገው ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኅብረት ባንዲራን በየኤምባሲያቸው እና የመንግስት ቢሮዎቿ ከፍ አድርገው ከሚያውለበልቡ ቀደምት ሀገራት መሀል ተጠቃሽ አይደለችም (ከጥቂት ኤምባሲዎቻችን ውጪ ማለት ነው)።ታዲያ አሁን የመጣው የመተባበር መንፈስን ይበልጥ አጠናክሮ ለመቀጠል ትልቅ እድል የመጣ ይመስላል። ፓን አፍሪካኒዝም ለችግር ግዜ ብቻ ሳይሆን ሁልግዜ በአፍሪካውያን ሊነሳ እና ሊተገበር የሚገባው መርህ ይመስለኛል። ኢትዮጵያውያን ስለ መርሁ በደንብ ተረድተው ብዙ ሊሰሩ የሚችሉበት መድረክ ነው ሲል ጋዜጠኛ ኤልያስ ያሳስባል።

ቅኝ ገዢዎችና ተስፋፊዎች ጥቁሮች የራሴ መብት፣ የግሌ ሀብት፣ የእኔ ሀሳብ የሚሉት ነገር እንዲኖራቸው አይፈልጉም።እኔ ካልኩት ውጭ በሚል የበታች አድርገው ረግጦ መግዛትን ፖሊሲያቸው አድርገው ኖረዋል። ይህ አብዝቶ ያስጨነቃቸው ጥቁሮች በሀገረ አሜሪካ የነፃነት ጩኸት ማሰማት ጀመሩ፤ የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ። ንቅናቄው በዋናነት የቅኝ ግዛት መስፋፋትን ወይም የነጮች የበላይነትን በመዋጋት የአፍሪካን አንድነት ለማጠናከር የታሰበ ነው። ፓን አፍሪካኒዝም በአሜሪካ ምድር ይጠንሰስ እንጂ፤ የንቅናቄው መንፈስና ብርታት ኢትዮጵያ እንደነበረች ታሪክ ያወሳል።

ለዚህም ነው ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኩራት የጀግንነት ተምሳሌት ተደርጋ የምትገለጸው። የፓን አፍሪካኒዝም ግቡ ጠንካራ አፍሪካዊት ሀገር መመስረት ነበርና ለነጮች ያልተንበረከከችና ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ ነፃነቷን ጠብቃ ያለች ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗን አምነው ተንቀሳቅሰዋል። የአፍሪካ ሀገሮች የማዕዘን ድንጋይ ሆና መታየቷ ከጎኗ እንዲቆሙ አድርጓቸዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ነፃነት የአፍሪካ ብሎም የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ተደርጎ ይወሰዳል። በተመሳሳይ ጉዳቷን ጥቃቷም የእነርሱ ሕመም ነው። አሁን ያለው ኢትዮጵያን ደካማና የተበተነች ሀገር በማድረግ የአፍሪካን ነፃነት ለመንጠቅ እየተደረገ ያለውን የእጅ አዙር ጦርነት በፓን አፍሪካኒዝም መንፈስ መዋጋት እንደሚያስፈልግ ምሁራን ለኢዜአ ይናገራሉ።

በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር ዓለማየሁ አብርሃም እንደሚሉት ኢትዮጵያ ጥቁር ሆና በታሪክ ነጮችን በማሸነፍ የጥቁሮችን ነፃነትና የእችላለሁ መንፈስ በደማቅ ቀለም ጽፋለች። ይህ ደማቅ ታሪኳ ለመላው ጥቁሮች የአንድነት እንቅስቃሴ (ፓን አፍሪካኒዝም) ስንቅ ነው ይላሉ። ኢትዮጵያ ያላት ጀግንነት በታሪክ የሚቀር በትውልድ የሚቋረጥ አይደለም ያሉት መምህር አለማየሁ፣ በአድዋ ጦር ግንባር ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘፋናቸውን ትተው በመዝመት ተዋግተው ጣሊያንን አሳፍረዋል።

ምዕራባውያን እነርሱ እንደፈለጉ የሚያዙትና የሚጋልቡት መንግሥት በአፍሪካ እንዲፈጠር ይፈልጋሉ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ አይሆንም የእኛ ጉዳይ እኛ እናውቃለን በማለት ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትን መወከሏ ምቾት አልሰጣቸውም ይላሉ ምሁሩ። ቀድሞ ኢትዮጵያን በመበተን አፍሪካን እንደፈለጉ የማድረግ ዓላማ ይዘዋል። የፓን አፍሪካኒዝም አስተሳሰብ ማራመድ ያስፈልጋል ይላሉ መምህር ዓለማየሁ። በሌላ በኩል በዩኒቨርሲቲው የሥነ ዜጋ ትምህርት ክፍል መምህር ሙሉቀን አየለ እንደሚሉት፤ ሌሎችን ለነፃነት የምታስተባብር አፍሪካዊት ሀገር በክብር እንድትኖር በነጮች አይፈለግም። በመሆኑም ፓን አፍሪካኒዝም በተጠናከረ እንቅስቃሴ መጀመር አለበት። እንደ ግለሰብ ሳይሆን እንደ ሀገር አፍሪካን እየተከፋፈሉ ግዛታቸውን ሲያስፋፉ አፍ እያላቸው የማይናገሩ፣ አቅም እያላቸው ምንም የማይቻሉ አድርገው ይገዙ ነበር።

ዛሬ ደግሞ በቀጥታ መግዛትና መዝረፍ አልቻሉም። ያመረቱትን ሸቀጥና የፖለቲካ ፍልስፍናና እሳቤዎቻቸውን ሊያራግፉብን ይሻሉ። እኛ እናውቅላችኋለን፤ የሚበጃችሁ የእኛን ሀሳብ መቀበል ለእኛ ታዛዥ መሆን ነው ሊሉን ይዳዳሉ። ግን ይሄ ዘመን ያለፈበት ጉዳይ መሆኑን ሊረዱት አልቻሉም ወይም አልፈለጉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አድዋን በአጎዋ አይለውጥም። ማንነቱንም አሳልፎ አይሰጥም። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊ ነውና! አዎ ጮኽ ብለን እንናገራለን አፍሪካ በእጅ አዙር ቅኝ አስተዳደር አትገዛም። የራሷ ፍልስፍና፣ የራሷ ማንነት ያላት አህጉር ናትና! ለዚህ ደግሞ በቀደምት አፍሪካውያን የተጠነሰሰው ፓን አፍሪካኒዝም ማሳያ ነው። ጊዜው የአፍሪካ ትንሳኤ የሚታወጅበት ነው። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ዋጋ በመክፈል ላይ ናት ይላሉ አስተያየት ሰጪው።

ወቅታዊ የአፍሪካ ችግሮችን ለመፍታት በፓን አፍሪካኒዝም መንፈስ መሰባሰብና ለጋራ ጉዳዮች በጋራ መሥራት ያስፈልጋል። ዲፕሎማቶቹ ፓና አፍሪካኒዝም፤ መላው አፍሪካዊ አንዱ ለሌላው የቆመና ተቀራራቢ ታሪክ፣ ባሕልና ተመሳሳይ ችግሮች ያሉበት ሕዝብ መሆኑን አመላካች አስተሳሰብ ነው። በዚህ አስተሳሰብ በመቃኘትም አህጉሪቱ ከጸጥታ መደፍረስ ጀምሮ የሚፈትኗትን የተለያዩ ችግሮች ለመፍታት የጋራ ርብርብ እንደሚያስፈልግ ኢዜአ ያነጋገራቸው ዲፕሎማቶች ይገልጻሉ።

የዛምቢያው ዲፕሎማት ዶክተር አንድሪው ሲሉሜሲ፤ ፓን አፍሪካኒዝም አፍሪካውያኖች አንድ መገኛ ያላቸው መሆኑንና እጣፈንታቸውን በጋራ ሊወሰን የሚችል መሆኑን፤ በተጨማሪ አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ያላቸውን ሥፍራ የሚያመላክትና በጋራ በመሥራት የምንፈልጋትን አፍሪካ እውን ለማድረግ የሚያነሳሳ፤ አፍሪካ የሚያጋጥማትን ችግሮች ለመፍታት በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤ የተቃኘ አጋርነትና አንድነት በመፍጠር ለጋራ ዓላማ መረባረብ እንደሚገባ፤ የምንፈልጋትን አፍሪካ እውን ለማድረግ በተናጠል ሳይሆን በጋራ ጉዳዮች ላይ ተቀራርበን መስራት እንደሚጠበቅበን ሊሰመርበት ይገባዋል።

ከዚህ አኳያ የአፍሪካ ኅብረት አህጉሪቱን ሊጠቅማትና ትልሟን ሊያሳካላት የሚችሉ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ መንቀሳቀስ እንዳለበት ጠቁመዋል።

ደቡብ ሱዳናዊው ዲፕሎማት ጆን ዮሄንስ በበኩሉ ፓን አፍሪካኒዝም የአፍሪካ ሕዝቦች በተለያዩ አኅጉራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ እንዲቆሙና ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያደርግ እሳቤ መሆኑን፤ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት አህጉሪቱን በተለያየ መልኩ እየፈተኑ ያሉትን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት በጋራ መረባረብ እንደሚገባም፤ ወጣቶችን ተሳታፊ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ፤ ይህን ማድረግ ከተቻለ አኅጉሪቱ ላይ በርካታ ለውጦች ማምጣት እንደሚቻል፤ በተለይም የአፍሪካ ኅብረት እንዲህ ያሉ አኅጉራዊ አጀንዳዎች ላይ ከዚህ ቀደም የነበረውን ሚና ይበልጥ በማጠናከር ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ሲል አሳስቧል።

ሻሎም ! አሜን።

# ‹‹የተፋሰስ ልማት ለአካባቢው አማራጭ የሌለው እንደሆነ አርሶአደሩም ሆነ አርብቶአደሩ ተገንዝባል››

- ወይዘሮ ኢክራም ጠሐ
የምዕራብ ሐረርጌ ዞን አስተዳዳሪ



**ስምስም ምንግሥቱ**

በኦሮሚያ ከሚገኙ 23 ዞኖች መካከል አንዱ ምዕራብ ሐረርጌ ነው። 15 ወረዳዎች እና 512 ቀበሌዎች አሉት። አዋሳኞቹም ምሥራቅ ሸዋ፣ ምሥራቅ አርሲ፣ ባሌ፣ ሶማሌና አፋር ክልሎች ናቸው። ምዕራብ ሐረርጌ በመካከል ላይ የምትገኝ የወጪ ንግድ ማዕከል (ኢምፖርት ኤክስፖርት ኮሪዶር) ናት። በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋም ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ጫት ነው። የህዝቧ የኑሮ እንቅስቃሴም የተመሰረተው በዚሁ የጫት ንግድ ገቢ ነው። የቡና ልማትም ሌላው የአካባቢው የኢኮኖሚ ምንጭ ነው። የተለያዩ የሰብል ልማቶችም ይከናወናሉ። ከነዚህ የሰብል ልማቶች ደግሞ የበጋ ቆላ ስንዴ መስኖ ልማት ለዞኑ ተጨማሪ መሆኑም እንደ አንድ ትልቅ እመርታ ተወስዷል።

በነዚህ የልማት እንቅስቃሴዎች፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶችና ከወቅታዊ ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በተለይም የአካባቢ ሰላምንና ደህንነትን በማስጠበቅ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት የምዕራብ ሐረርጌ ዞን አስተዳዳሪ ከወይዘሮ ኢክራም ጠሐ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- በምዕራብ ሐረርጌ ዞን የግብርና እና አጠቃላይ የልማት ሥራ እንቅስቃሴና ውጤታማ የሚባሉ ተግባራትን ቢገልጹልን፤**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** በዞኑ በግብርናው በአረንጓዴ አሻራ ተፋሰስ ልማት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በተለይም ባለፉት ሶስት ዓመታት፤ ለአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ልዩ ትኩረት በመስጠት፤ የተቀናጀና የተናበበ ሥራ በመሥራት ስኬት ማስመዝገብ ተችሏል። በዚህ የተፋሰስ ልማት ሥራም ተራቁተው የነበሩ የዞኑ ተራራማ አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ ማድረግ ተችሏል። የደን ሽፋናቸውም እየተሻሻለ መጥቷል። ደርቀው የነበሩ ምንጮች አሁን ላይ ወደነበሩበት ተመልሰዋል። ለአብነትም ባሮጨርጨር ደርቆ ነበር። አሁን ላይ ተመልሶ በብዛት የአሣ ምርት ማግኘት ተችሏል። ይህ አካባቢም በክልሉ መንግሥት በኢኮ ቱሪዝም እውቅና ስለተሰጠው የማልማቱ ሥራ ተጠናክሯል። የተሰራው ሥራም ተጨባጭ ለውጥ ያስገኘ በመሆኑ በጥሩ ተሞክሮ ተወስዷል። እንዲህ ያሉ በጎ ተሞክሮዎች መቀጠል እንዳለባቸውም ከተሰሩት የሥራ ውጤቶች ግንዛቤ መያዝ ተችሏል።

ምዕራብ ሐረርጌ ዝናብ አጠር ከሚባሉ አካባቢዎች አንዱ ሆኖ ሲሆን በአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በተከታታይ ዓመታት የዛፍ ችግኞች በመተከላቸው አካባቢው ላይ የሚስተዋለው የዝናብ እጥረት እንዲሚሻሻል ተስፋ ያሳደረ ሥራ ሆኗል ። የዝናብ መጠን መጨመር ለግብርናው ብቻ ሳይሆን፣ የአካባቢውን የመጠጥ ውሃ ችግርንም ስለሚፈታ የተፋሰስ ልማት ለአካባቢው አማራጭ የሌለው እንደሆነም አርሶአደሩም ሆነ አርብቶአደሩ ተገንዝቧል።

የተፋሰስ ልማት ስራ እንደሀገር የተቀመጠውን አቅጣጫ ለመተግበር እኛ በዞናችን ቀድመን ነው ሥራ የጀመርን ሲሆን በየዓመቱም በተራራማ አካባቢዎች የተፋሰስ ልማት ስራዎች ይሰራሉ። ከዛፍ ችግኝ ተከላዎች በተጨማሪ የተለያዩ የፍራፍሬ ልማት ሥራዎችም ጎን ለጎን እየተከናወነ ይገኛል። እነዚህ ተጨማሪ የልማት ሥራዎች ገቢ ማስገኛዎች ወይንም የአካባቢ ስነምህዳርን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን፤ ማህበረሰቡ አመጋገቡ የተመጣጠነ እንዲሆን የሚያስችሉ ጭምር ናቸው።

በግብርናው ዘርፍ፤ በአካባቢው የተለያዩ የሰብል ልማቶች ቢከናወኑም እስከ አሁን በስንዴ ልማት አካባቢው አይታወቅም ነበር፤ ስንዴ ባለመመረቱም በተለይም በቆላማው የዞኑ ወረዳዎች ለሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ስንዴ በእርዳታ ነበር እንዲያገኙ ሲደረግ የነበረው።

አሁን ላይ ግን እንደ ሀገር ታቅዶ ወደ ትግበራ የተገባው የበጋ ቆላ ስንዴ መስኖ ልማት በዞናችንም ለመተግበር መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ ላይ አመራሩ፣ ባለሙያው፣ አርሶአደሩም ሁሉም በጋራ ተወያይተው መግባባት ላይ በመድረስ ወደ ሥራ የተገባው በመሆኑ በረሀ ውስጥ ስንዴ እንዲለማ እያስቻለ ነው።

በተለይም በዘንድሮ በጀት ዓመት በዞኑ ወደ 40 ሺ 500 ሄክታር መሬት ላይ የስንዴ ልማት እንዲከናወን ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን እቅዱን ከግብ ለማድረስ የልማት ሥራው ከዓመት ዓመት እየጨመረ በመምጣቱ አሁን ላይ ውጤት ማየት ተጀምሯል። በ2014 በጀት ዓመት በ17ሺ ሄክታር መሬት ላይ፣ በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ 34ሺ ሄክታር ላይ ነበር ልማቱ የተከናወነው። በዚህ በጀት ዓመት የልማቱ ሥራ ቀድሞ ነው የተጀመረው። ስንዴውም ቀድሞ መድረስ ችሏል። በአሁኑ ጊዜም አርሶአደሩ የአጨዳ ሥራ ላይ ይገኛል።

ሌላው በግብርናው ዘርፍ በሌማት ትሩፋት የሚከናወነው ሥራ ሲሆን ከብት ማድለብ፣ በንብ ማነብ የማር ልማትና በሌሎችም በሰፊው እየተከናወነ ይገኛል። አጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ እየተሰራ ያለው ሥራ ተስፋ ሰጪና የሚያበረታታ እንደሆነ ነው የሥራ ግምገማችን የሚያሳየው። ግምገማችን በዚህ መልኩ ቢያስቀምጥም ክፍተቶች መኖራቸውንና አሁን እየተሰራ ካለው በላይ ስኬት ለማስመዝገብ በልማቱ ላይ ያለውንም በማስተባበር የተጠናከረ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል።

**አዲስዘመን፡- በማኅበራዊ ዘርፍ በትምህርት፣ በጤና እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራትና ተደራሽነቱን እንዴት ይገልጹታል?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** ማኅበረሰቡን በማሳተፍ ሰፊ የትምህርት ቤት ግንባታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡ በዞኑ ከዚህ ቀደም የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች አልነበሩ በመሆኑና አስፈላጊነቱም ስለታመነበት የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማስተባበር ወደ 999 መዋዕ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች በመገንባትና ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ እድሉ ያልነበራቸው ከከተማ ራቅ ያሉ አካባቢዎች እየተጠቀሙበት ነው።

እንደ ሀገር የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በመንግሥት የተያዘውን አቅጣጫ ተግባራዊ በማድረግ የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች ቅድሚያ እንዲያገኙ የተሰራ ሲሆን በዚህም የትምህርት ጥራትን ከታች ጀምሮ ለማስጠበቅ ዞኑም የድርሻውን ለመወጣት ችሏል። ወደላይ ያሉት ተማሪዎች በትምህርታቸው ጠንካራ እንዲሆኑም የተለያዩ ማበረታቻዎች እዲደረጉም ጥረት እየተደረገ ነው።

በትምህርታቸው የተሻሉ ተማሪዎችና ሴቶች ተለይተው የተለየ እገዛ ለማግኘት እንዲችሉ ልዩ ትምህርት ቤት (ስፔሻል ክላስ) በማዘጋጀት ሥራዎች እየተሰሩ ነው።

እንደ ሀገር የትምህርት ጥራት ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ያለ ቢሆንም በ 2015 ዓ.ም በተሰጠው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው ያለፉ 4 ነጥብ 9 በመቶ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲገቡ ሆኗል። በነገራችን ላይ ይህ ውጤት እንደ ዞናችን አበረታች የሚባል ነው።

የትምህርት ጥራት መጓደል የተማሪው፣ የቤተሰብ ችግር ብቻ ተደርጎ መውሰድ የለበትም። የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ ጭምርም ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ አመራር በትምህርት የሚመዘገበውን ስኬትም ሆነ ውድቀትን ኃላፊነት እንዲወሰድ አቅጣጫ ተቀምጧል። የትምህርት ጉዳይ የበለጠ ትኩረት እንደሚስፈልግ ካለፉ ተሞክሮዎችም ትምህርት መውሰድ ይቻላል። የትምህርት ጉዳይ የመንግሥትም ትኩረት በመሆኑ አንጻር ዞናችንም የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ ትምህርት ቤቶችን ከታች ጀምሮ ገንብቶ ተደራሽ በማድረግና በመማር ማስተማሩም ትኩረት ሰጥቶ ለመንቀሳቀስ በአመራሩ በኩል ቁርጠኛ አቋም ይዟል።

በጤናው ዘርፍም በሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተሰሩት ሥራዎች ውጤት አስገኝተዋል። በተለይም ማኅበረሰቡ የጤና መድን ተጠቃሚ እንዲሆን ከፍተኛ ሥራ በመሰራቱ ብዙዎች አገልግሎቱ ለቤተሰባቸው ዋስትና እንደሆነ ግንዛቤ በመያዝ አባል ሆነዋል። በዚህም በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ 23 ዞኖች መካከል ምዕራብ ሐረርጌ በተሻለ አፈፃፀም ተጠቅሷል።

ተጠቃሚው በአገልግሎት አሰጣጥ የሚያነሳውን ቅሬታም ለማስተካከል ያሉ ክፍተቶችን በውይይት ለመፍታት ጥረት ተደርጓል። ከጤና አገልግሎት ጋር በተያያዘ ትልቁ ችግር በሚፈለገው መጠንና አይነት የመድኃኒት አቅርቦት አለመኖር በመሆኑ ማኅበረሰቡ የጤና መድን አባል በመሆን ግዴታውን ተወጥቶ ግን በሆስፒታሎች ውስጥ መድኃኒት እየቀረበለት አይደለም።

መድኃኒት ፍለጋ የግል አቅራቢዎች ጋር እንዲሄድ እየተገደደ ነው፡፤ ይህም ቅሬታ እየፈጠረ በመሆኑ አስተዳደሩ አጀንዳ አድርጎ በተለያየ ጊዜ እየመከረበት አቅርቦቱ የሚሻሻልበት መንገድ እንዲፈጠር ጥረት ቢያደርግም ካለው ፍላጎት አንጻር አቅርቦቱ ሊመጣጠን አልቻለም። በመድኃኒት አቅርቦት በኩል የሚሰጠው ምላሽ አጥጋቢ አይደለም። በግንባታ በኩልም በተከናወኑ የተለያዩ ተግባራት፤ በወረዳዎች ተደራሽ ለማድረግ የጤና ኬላዎች ተሰርተዋል።

በማኅበራዊ አገልግሎትም እንዲሁ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል። በዚህ በኩል ረዳትና የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ነዋሪዎች ማኅበረሰቡን በማስተባበር የቤት እድሳትና ግንባታ ተከናውኗል። በቤተሰብ አቅም ማነስ የትምህርት ቁሳቁስ ላልተሟ ላላቸው ተማሪዎችም በዞኑ በሚገኙ 15 ወረዳዎችና አምስት ከተሞች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ማኅበራዊ አገልግሎቱ በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ በመከናወኑ ውጤት ተገኝቶበታል። ብዙ የአካባቢው ማኅበረሰብም ተጠቃሚ ሆኗል። በመንግሥት በጀት መሸፈን የማይቻል ሥራ ነው በማኅበረሰብ ተሳትፎ የተከናወነው። የበጎ አድራጎት ሥራ በኦሮሚያ ክልል ሕግ ሆኖ በመጽደቁም የበለጠ ተጠናክሯል።

ማኅበረሰቡ እንደክፍተት ከሚያነሳቸውና ከሚያማርራቸው የፍትህ መጓደል አንዱ ነው። የማኅበረሰብ ቅሬታን መሰረት በማድረግ ሰዎች ፍትህ ለማግኘት ፍርድቤት ተመላልሰው ረጅም ጊዜ የወሰደባቸውን ጉዳይ በማኅበራዊ ፍርድቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ በማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ ውጤትም እየታየበት ሲሆን ይህ አሰራር ደግሞ ሰዎች ትክክለኛ ፍትህም እንዲያገኙ፣የገንዘብ ወጪና ጊዜያቸውን እንዲቆጥቡ አስችሏል።

በማኅበራዊ ፍርድ ቤት ውስጥ የዳኝነቱን ሥራ የሚሰሩትም በአካባቢያቸው ያለውን የማኅበረሰቡን ችግር ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው በቀላሉ መፍትሄ የሚሰጡ ናቸው። በተለይም በሀሰት ምስክርነት በዳዩ ተጠቃሚ፣ ተበዳዩ ደግሞ ተጎጂ የሚሆንበት በስፋት የሚስተዋልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ማኅበራዊ ፍርድቤቱ ይሄን ክፍተት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹የተፋሰስ ልማት ለአካባቢው...



ከገጽ 7 የዞረ

በማስቀረት የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል።

ሰዎች ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ማኅበራዊ ፍርድቤቱ ሰዎች በሀሰት ሊምሉ በማይችሉባቸው ነገሮች መሀላ እንዲፈጽሙ ነው የሚያደርጓቸው። እነዛ መሀላ በማይፈጽሙባቸው ነገሮች ማንም ደፍሮ ለመማል አይሞክርም። የባህል ፍርድ ቤቱ በዚህ መንገድ በመጠቀም መደበኛ ፍርድ ቤት ሊፈታ ያልቻለውን ፍትህ በመስጠት ለማኅበረሰቡ በተለይም ለተበዳይ እፎይታን ሰጥቷል። የዚህ ማኅበራዊ ፍርድቤት ሌላው በጎ ተግባር ወይም እንደ መልካም ነገር የሚወሰደው በትክክለኛው ፍርድ በዳይ ቅጣት ሲበየንበት ተበዳይ ደግሞ ትክክለኛውን ፍትህ ሲያገኝ፤ የበዳይና የተበዳይነት ስሜት ተፈጥሮ አይሸኙም። ተቀያይመው እንዳይሄዱ ነው የሚደረገው። ማኅበራዊ ፍርድቤቱ ሁለቱንም አስታርቆ ነው የሚሸኛቸው።

እንዲህ ያለው አሰራር በመደበኛው ፍርድቤት የተለመደ አይደለም። ፍትህ ፈላጊዎች በማኅበራዊ ፍርድቤት መዳኘት ከጀመሩ ወዲህ በሀሰት መመስከርን ወይንም ውሸትን አስቀርቷል። የመደበኛ ፍርድቤት ሥራንም በማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። እንዲህ ዘርፈብዙ ጥቅም እየሰጠ ያለው ማኅበራዊ ፍርድቤት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያስፈልጋል። ማኅበራዊ ፍርድቤቶቹ ተልእኮአቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ፀሐፊ ተቀጥሮላቸዋል። የሚሰሩበት ቢሮም ተሰጥቷቸዋል። ለተገልጋዩ የሚሰጡት ደረሰኝም ተዘጋጅቶ እየቀረበላቸው ነው።

ማኅበራዊ ፍርድቤቶች የሕዝቡን የፍትህ ጥያቄ እንዲመልሱ፣ የማኅበረሰብ የበጎ አገልግሎት ተግባርም ተጠናክሮ ዘላቂ እንዲሆን እውቅና ተሰጥቷቸዋል። የኦሮሚያ ክልል መንግሥትም ሕግ ሆኖ ሥራ ላይ እንዲውል በአዋጅ አጽድቆታል። እስካሁን በተከናወኑት ሥራዎችም የሕዝብ እርካታ መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል።

የመደጋገፍ ባህልን ለማሳደግም" ቡሳጎኖፋ" የሚባል አሰራር በክልሉ መንግሥት በአዋጅ ፀድቆ እየተሰራበት ሲሆን ቡሳጎኖፋ እንደቀይም መስቀል ማህበር አይነት ነው። አርሶአደሩ፣ አርብቶአደሩ፣ ነጋዴው፣ በየደረጃው ያለው ሕብረተሰብ ሁሉ አባል ሆነው በጋራ የመደጋገፍ ሕብረት ይፈጥራሉ። ለዚህም አባላት የሚጠበቅባቸውን ክፍያ መፈጸም ይኖርባቸዋል። በአይነት ደግሞ ከእያንዳንዱ አባል እህል ይሰበሰባል።

በግለሰብ ወይንም በወረዳ ደረጃ የኢኮኖሚ ችግር ቢያጋጥም መንግሥት አይጠበቅም። ቀድሞ ከአባላት ከተሰበሰበው ገንዘብና እህል ለተቸገረው ወይንም ለሌላው ድጋፍ ይደረጋል። ችግሮች ሲያጋጥሙ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የተቀመጠ ዘዴ በመሆኑ ሰዎች ብዙ ጉዳት ሳይደርስባቸው ተጠቃሚ ይሆናሉ። በዞኑ በትምህርትቤቶች የተተገበረው ምገባም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው።

ሌላው"" ጋቸናሲርና የሚባለው ነው። ይህ ማለት ከሕብረተሰቡ ውስጥ ተመልምሎ ስልጠና ወስዶ የወረዳውን፣ የቀበሌውን፣ አጠቃላይ የማኅበረሰቡን ሰላምና ደህንነት የሚጠብቅ ማለት ነው። ጋቸናሲርና ለሰላሙ እራሱ ባለቤት የሚሆንበት አሰራር ነው። ሰላሙን የሚያደፈርሰውን ተባብሮ በአንድነት ከውስጡ የሚያስወግድበት ነው።

ምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሰላም ዙሪያ፤ ከፀጥታውም ሆነ ከፖለቲካ አመራሩ ጋር በተቀናጀ እየተሰራ ሲሆን፣ በየጊዜው ሥራዎች እየተገመገሙና አቅጣጫም እየተቀመጠ የጥበቃ፣ የፍተሻ፣ የኦፕሬሽን ሥራዎች ተጠናክረው እየተከናወኑ ነው። በዚህ ረገድ አስፈላጊው መስዋዕትነት እየተከፈለ ነጋዴውም ንግዱን እንዲያከናውን፣ ተማሪውም ተምሮ እንዲገባ በአጠቃላይ ሕዝባችን ከስጋት ነፃ ሆኖ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ እየተሰራ ነው። ይህም በመሆኑ ሕዝቡ ያለአንዳች ስጋት 24 ሰዓት በመንቀሳቀስ የእለት ተእለት ተግባሩን እየተወጣ ይገኛል። ይህም የጠንካራ የፖለቲካ ሥራ ውጤት ነው። ሕዝቡም ከፀረሰላም ኃይሎች ጋር የሚያብሩትንና ለመቀላቀል የሚንቀሳቀሱትን ለመንግሥት አካል መረጃ በመስጠትና በማጋለጥ እያደረገ ያለው እገዛም ከግምት ውስጥ የሚገባ በመሆኑ ሕዝቡም የራሱን ድርሻ በመውሰዱ ምስጋና ይገባዋል።

ዞናችን የወጪ ንግድ (ኢምፖርት ኤክስፖርት) ኮሪደር በመሆኑ፤ በፀጥታ በኩል ልዩ ትኩረት ነው የተሰጠው። ፀጥታ በማደፍረስ የሚፈታተኑ ስላሉ አጎራባች ከሆኑት ሶማሌና አፋር ክልሎችና ከሌሎችም ጋር ምክክር በማድረግ በጋራ እየሰራን እንገኛለን። በዞናችን ውስጥም ቢሆን በክላስተር ወረዳዎች እርስበርስ በሰላም ዙሪያ መረጃ በመለዋወጥ፣ በገንዘብ፣ በሰው ኃይል እየተረዳዱ ይረባረባሉ። በልማት ደግሞ እየተፎካከሩ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ነው ያለው።

ጠንካራ የሆኑ ሚሊሻዎችንም በስልጠና በማብቃትና በማስታጠቅ ጭምር የአካባቢው ሰላም የበለጠ እንዲረጋገጥ እየሰራን እንገኛለን። ይህ ሁሉ ሥራ ለሰላም የተሰጠውን ቅድሚያ የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ሰላም ከሌለ ስለ ልማትና እድገት ማሰብም መስራትም አይቻልም። ውሎ መግባትም ስጋት ነው ።

በያዝነው በጀት ዓመት የስድስት ወር ግምገማችን የሚያሳየው ምዕራብ ሐረርጌ፤ በሰላምና በልማት ሥራ በተለይም ተነሳሽነት በመውሰድ በገጠርና በከተማ ክላስተር፣ እንዲሁም በማኅበራዊ ዘርፍ ክላስተርና በገቢ ማሰባሰብ በዞን ደረጃ በሶስተኛ ደረጃ ነው የሚገኘው።

እስካሁን የሰራነው ስራ የሚያበረታታ ቢሆንም በቂ አይደለም። የበለጠ አቅማችንን መፈተሽ አለብን። ሰፊ የሆነ የሰው ኃይል፣ በሀብት በኩል እንዲሁ የተፈጥሮ ሀብቶች አሉን። ይህን ፀጋ ይዘን ወደ ሥራ በመቀየር ሕዝባችን ከድህነት ውስጥ እንዲወጣ ማድረግ ይኖርብናል።

በተለይም በበጋ ቆላ ስንዴ ልማት በዞኑ እየተመዘገበ ያለው ውጤት እጅግ አበረታች ነው። መንግሥት ለውጭ ገበያ ስንዴ ለማቅረብ በያዘው እቅድ እንደምዕራብ ሐረርጌ ኮታ ተሰጥቶን ተሳትፈናል። እንዲህ ያለው ነገር በጣም የሚያበረታታና የሚያነቃቃ በመሆኑ ሕዝባችንን እያወያየን በጋራ እንቀሳቀሳለን። ለልማቱ ትልቁ አቅም ሕዝቡ ነው። ጠንካራ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ከተቻለ ልማትን ማፋጠንና እድገት ማምጣት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ዞኑ የምድር በረከት ፀጋዎችም እንዳሉት ይታወቃል። በዚህ በኩልስ ምን ተግባራት ተከናወኑ?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** በዞኑ ለጌጣጌጥ እና ለኢንደስትሪ ግብአት የሚውሉ የማዕድን ሀብት ክምችት አለ። ሆኖም ግን ለማዕድን ሥራ የሚያስፈልጉ ማሽኖች ባለመኖራቸው ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ የለም። ማሽን ለማቅረብ አቅም አለመኖሩ ደግሞ ክፍተቱን አስፍቶታል። ስራው ቢኖር ሰፊ የሰው ኃይል በመያዝ ያግዝ ነበር። ወደፊት ግን በማዕድን ልማት ላይ 60 በመቶውን ባለሀብቱ ቀሪውን ደግሞ ወጣቶች የሚጠቀሙበት አሰራር ኖሮ ልማቱ እንዲከናወን ከማዕድን ቢሮ ጋር ተነጋግረናል።

**አዲስ ዘመን፡- ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር በኩል ዞኑ ምን አይነት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** ሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ በስፋት እየተሰራ ያለው በቆላማው የዞኑ አካባቢዎች ነው። መሬት በስፋት ያለው በቆላማ አካባቢ በመሆኑ ነው በአካባቢው ላይ ትኩረት የተደረገው። በዞናችን ወጣቶች ተደራጅተው በበርበሬ ልማት ላይ እንዲሰማሩ እየተደረገ ሲሆን አሁን ላይ ያመረቱት በርበሬ ለጅቡቲ ገበያ እየቀረበ ነው። በከተማ ግብርናም በከብት ማድለብ፣ ዶሮ በማርባት፣ ንብ ማነብና በሌሎችም የልማት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩም ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሮላቸዋል።

በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ላለው ሥራ ፈላጊ ወጣት እስካሁን የተሰሩት ስራዎች አመርቂ ናቸው ብሎ ለመናገርም አያስደፍርም። በመሆኑም በማኅበር በማደራጀት ሥራ እንዲፈጠርላቸው ማድረግ ላይ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል። ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረቁ፣ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሥራ ፈላጊዎች ወጣቶችን እንዲሁም በዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ መልቀቂያ ፈተና ውጤት ያልመጣላቸውን የሥራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ያሉ አምራች ኢንደስትሪዎች ምዕራብ ሐረርጌ ውስጥ አለመኖራቸውም ሰፊ የሥራ እድል እንዳይኖር አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- ዞኑ ላይ ምን አይነት የኢንቨስ ትመንት እድሎች አሉ? ባለሀብቶችን ለመሳብ የተከናወኑ ተግባራትስ ምን ይመስላሉ?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** በዞኑ በግብርና ሥራ ግንባር ቀደም የሆኑ አርሶ አደሮችንና በማይክሮ የተደራጁትን ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገሩ የማድረግ ሥራ ተጀምሯል። በክልል ደረጃም ተቀባይነት አግኝቷል። በቁጥር ወደ 60 የሚሆኑ ተለይተው ፍላጎታቸው ታይቶ የመስሪያ ቦታ ከማቅረብ ጀምሮ አስፈላጊው ነገር ተመቻችቶላቸው ወደ ሥራ ገብተዋል። ይህ በቂ ባለመሆኑ የተጀመረው ሥራ የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ሁኔታም አቅጣጫ በመቀመጡ እንቅስቃሴው ይቀጥላል።

**አዲስ ዘመን፡- በቱሪዝም ኢንደስትሪው በኩል ያለው እንቅስቃሴስ እንዴት ይገለፃል?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** በዞኑ ዋሻዎች ፣ የተለያዩ የዱር እንስሳት፣ የመስህብ ስፍራዎች፣ እድሜ ጠገብ የሆኑ ከቤተክርስቲያን ጋር የተያያዙ ታሪኮች፣ ቢታወቁና ቢወጡ የቱሪዝም መዳረሻ የሚሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶች አሉ። ሆኖም ግን በሚፈለገው ልክ በዚህ ዘርፍ እንቅስቃሴ አልተደረገም። በቱሪዝም ዘርፍ መስራት እንዳለብን ግን እንገነዘባለን።

**አዲስ ዘመን፡- መሠረተ ልማትን ከማሟላት አንጻር የተሰሩ ሥራዎች ምን መልክ አላቸው?**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** በመብራት ኃይል አቅርቦት በኩል ከፍተኛ የሆነ ችግር አለ። ከ40 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ማሰራጫ (ሰብስቴሽን) አለው። በቂ የሆነ አቅም ስለሌለው የሚገኘው ኃይል ደካማ ነው። አደራጅተን ወደ ሥራ ያስገባናቸው አብዛኞቹ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚፈልጉ ናቸው። በዚህ ረገድ የኃይል መቆራረጡ ተጽዕኖ እየፈጠረ ነው። አስተዳደሩ ለሚመለከተው አካል በየጊዜው አቅርቦ ምላሽ በመጠበቅ ላይ ይገኛል።

በመንገድ መሰረተ ልማት በኩልም ደረጃዎች የማሳደግ ስራ የሚፈልጉ ናቸው። ሆኖም በመንግሥት በኩል አዲስ በጀት ባለመያዙ የመንገድ ሥራው ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ድልድዮች ግን ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ እናመሰግናለን።**

**ወይዘሮ ኢክራም፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማዘጋጀት ባለሃብቶችን የምትጋብዘው ድሬዳዋ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እንድታስመዘግብ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ እንደሚገባ ይታመናል። በተለይም የሥራ-አጥ ቁጥሩ እየጨመረና የዋጋ ንረቱ እያሻቀበ ባለበት በዚህ ወቅት ወደ ኢንቨስትመንት የሚመጡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማበራከት ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም። ይህን የተረዳው የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በከተማው ያለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ትርጉም ያለው ሥራ እየሠራ ይገኛል።

በንግድ እንቅስቃሴዋ ትልቅ ዝና ያላትና የበረሃዋ ንግስት በመባል በምትታወቀው ድሬዳዋ ከተማ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ተከናውነዋል። ከተማ አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በኢንቨስትመንት ዘርፍ 250 የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት አቅዶ 244 ፈቃድ በመስጠት የዕቅዱን 90 በመቶ ማሳካት መቻሉን ተመላክቷል። የድሬዳዋ ኢንቨስትመንት የጥናትና ፕሮሞሽን ቡድን መሪ የሆኑት አቶ አበራ መንግሥቱ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ያለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አበረታች የሚባል ነው። አስተዳደሩ በዕቅድ ይዞ እየሠራቸው በሚገኙ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ሥራዎች የተሻለ አፈጻጸም አስመዝግቧል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ የዕቅዱን ከ90 በመቶ በላይ መፈጸም ችሏል።

በእነዚህ ወራት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል ሰፊውን ድርሻ የሚይዘው አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን መስጠት ሲሆን አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 500 የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም በስድስት ወር 250 ፈቃድ ለመስጠት አቅዶ ሲሰራ ቆይቷል። በመሆኑም በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለ244 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት የዕቅዱን 90 በመቶ አሳክቷል።

ቡድን መሪው እንደሚሉት፤ የተሰጡት የኢንቨስትመንት ፈቃዶች በአራት የተለያየ ዘርፎች የሚመደቡ ናቸው። እነሱም በማምረቻ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ 87፣ በአገልግሎት 140፣ በኮንስትራክሽን አራት፣ በግብርና 13 አጠቃላይ 244 የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል። ፈቃድ የወሰዱ ባለሃብቶች ያስመዘገቡት ካፒታልም 38 ቢሊዮን 873 ሚሊዮን 489 ሺ 400 ብር ነው።

ከተማ አስተዳደሩ ፈቃድ ከሰጣቸው መካከል አንዱ በውጭ አገር ለሚኖሩ የድሬዳዋ ተወላጅ ሲሆን፤ ይህም ከተማ አስተዳደሩ ትልቅ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል ተጠቃሽ ነው የሚሉት አቶ አበራ፤ እነዚህ የድሬዳዋ ተወላጅ የሆኑ ዲያስፖራዎች በትውልድ ቦታቸው ኢንቨስት ማድረግ እንዲችሉና አሻራቸውን እንዲያኖሩ በርካታ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን ያስታውሳሉ። የተለያዩ የማስተዋወቅ ሥራዎችም ተሰርተዋል። በመሆኑም በአሁን ወቅት ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ድሬ ናፍቆት በሚባል ፈቃድ ያገኙ ሲሆን፤ ይህም አፈጻጸሙን ከፍ ማድረግ ችሏል ይላሉ።

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙት የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ግንባታቸውን አጠናቅቀው ወደ ሥራ ሲገቡ በርካታ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ያመላከቱት አቶ አበራ፤ በቋሚነት 7ሺ242 ለሚደርሱ ዜጎች እንዲሁም በጊዜያዊነት 12ሺ653 ለሚደርሱ ዜጎች በድምሩ ለ19 ሺ 901 ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ነው ያሉት። የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካገኙ 244 የአገር ውስጥ ባለሃብቶች መካከል 184 ወንዶች፣ 31 ሴቶች እንዲሁም 29 የግል ማኅበራት ይገኙበታል።

ፈቃድ የወሰዱ እነዚህ ባለሃብቶችም በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው ሀገራዊ በሆነው የምጣኔ ሃብት ዕድገት ላይ የበኩላቸውን ድርሻ ያበረክታሉ ተብሎ ይታመናል። በተለይም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግና ተኪ ምርቶችን በማምረት ረገድ ኢንቨስትመንት ትልቅ ድርሻ አለው። በመሆኑም አሁን ላይ መሬት የተሰጣቸው ባለሃብቶች በቶሎ ወደ ሥራ የሚገቡበት መንገድ የሚመቻች መሆኑን ያስረዱት አቶ አበራ፤ ባለፈው በጀት ዓመት ስድስት የሚደርሱ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው ወደ ሥራ መግባት እንደቻሉ ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ወደ ሥራ የገቡት የተለያዩ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፤ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩት አራት በአገልግሎት ዘርፍም እንዲሁ ሁለት በድምሩ ስድስት ባለሃብቶች መሆናቸውን ያመለክታሉ። ዘንድሮም በተመሳሳይ ፈቃድ የወሰዱ ባለሃብቶች ቶሎ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ምርት መግባት እንዲችሉ ከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል ይላሉ።

‹‹ከተማ አስተዳደሩ ፈቃድ ከመስጠት ባለፈ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ ወደ ምርት እንዲገቡ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል›› ያሉት አቶ አበራ፤ ማንኛውም ባለሃብት ፈቃድ ወስዶ እንዲጠፋ ሳይሆን በፍጥነት ወደ ሥራ መግባት የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ከተማ አስተዳደሩ የሚያመቻች መሆኑን ያስረዳሉ። ከዚህ ቀደም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው መሬት ተሰጥቷቸው መሬቱን አጥረው የተቀመጡ 88 የሚደርሱ ባለሃብቶች እንደነበሩ ነው የጠቆሙት።

ከተማ አስዳደሩ እነዚህን ባለሃብቶች በማወያየት፤ ወደ ሥራ ለመግባት ማነቆ የሆነባቸው ችግሮች ተለይተው መፍትሔ በመስጠት በፍጥነት ወደ ሥራ መግባት አንዲችሉ ተደርጓል። የከተማ አስተዳደሩ ክትትልና ድጋፍ ተጠናክሮ የሚቀጥል በመሆኑ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት የሚኖረው አፈጻጸም የተሻለና መቶ በመቶ መፈጸም እንደሚቻል ያመለክታሉ።

‹‹ሰላም የኢንቨስትመንት መሰረት ነው፤ በተለይም ለኢንቨስትመንት ሰላም ወሳኝ ነው። ሰላም ከሌለ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት አይቻልም። ኢንቨስትመንት ማስፋት ካልተቻለ ደግሞ ዘላቂ የሆነ የምጣኔ ሃብት ዕድገት ማስመዝገብ አይታሰብም›› ያሉት አቶ አበራ፤ አስተዳደሩ ለኢንቨስትመንት ዘርፉ እየሰጠ ባለው ክትትልና ድጋፍ የበኩሉን ሚና እየተወጣ እንደሆነ ያነሳሉ። እንደ ሀገርም በሰላም ዙሪያ ብዙ ሥራ ሊሠራ ይገባል ሲሉ ይናገራሉ።

በዚህ ረገድም በግማሽ በጀት ዓመቱ ለተመዘገበው የኢንቨስትመንት ውጤት ከተማዋ ሰላማዊ በመሆኗ እንደሆነ ያመላከቱት አቶ አበራ፤ ከሌሎች ክልሎች በተሻለ ሁኔታ ድሬዳዋ ላይ ያለው ሰላም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን አፋጥኖታል ባይ ናቸው። ‹‹ትንሿ ኢትዮጵያ እንደሆነች የሚነገርላት ድሬዳዋ ሰፈር እንጂ ብሔር የላትም ይባላል። ለዚህም አንዱ ማሳያ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል 73 ያህሉ ድሬዳዋ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው›› ይላሉ። እነዚህ ሕዝቦችም በሰላም፣ በፍቅር፣ በመቻቻል፣ በመተሳሰብ፣ በአንድነትና በጋራ በመኖር ለሌች አብነት ሆነው መቆየታቸው ነው ያስታወሱት።

የመሰረተ ልማት ለኢንቨስትመንቱ አመቺ ሁኔታን መፍጠር ሌላው አብይ ጉዳይ መሆኑን አንስተው፤ ‹‹መንገድ፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ውሃ፣ ቴሌኮምና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በከተማዋ በመዘርጋት ባለሃብቶችን ለመሳብ ጥረት ተደርጓል›› ይላሉ። መሰረተ ልማቶች ማሟላት የቻለ የኢንዱስትሪ መንደር በከተማዋ መኖሩ ባለሃብቶችን የሚጋብዝ እንደሆነ ያስረዳሉ። በከተማ አስተዳደሩ ከተገነባው የኢንዱስትሪ መንደር በተጨማሪ ክላስተር ኮፕሬሽን መኖሩን ጠቅሰው፤ በእነዚህ መሰረተ ልማት በተሟላላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች ውስጥ አስተዳደሩ ሼዶችን ሰርቶ ለባለሃብቱ የሚያስረክብ ሲሆን፤ ባለሃብቱም በቀላሉ ገብቶ ማምረት የሚያስችለው ይሆናል ሲሉ ያብራራሉ።

በሌላ በኩል ከተማዋ ለወደብ ቅርብ መሆኗም ትልቅ ዕድል የፈጠረላት መሆኑን ይጠቁማሉ። ‹‹የጅቡቲ ወደብ ከድሬዳዋ በ313 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። አዲስ አበባ ደግሞ በ515 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ድሬዳዋ ለጅቡቲ ቅርብ ናት። ይህም ከተማዋን ለኢንቨስትመንት ምቹ አድርጓታል›› በማለት ይናገራሉ።

እንደ ቡድን መሪው ማብራሪያ፤ ድሬዳዋ ለጅቡቲ ለወደብ ቅርብ በመሆኗ ባለሃብቶቹ ማሽኖችን ሲያስገቡ በቀላሉ ማስገባት ይችላሉ። ሌሎች ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡና ለሚወጡ ምርቶችም እንዲሁ አመቺና ቀላል ነው። በተጨማሪም ድሬዳዋ በአራት ክልሎች የተከበበችና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ የተመቸ ሲሆን፤ ኦሮሚያ፣ ሱማሌ፣ ሐረሪና አፋር ክልሎች ድሬዳዋን አካበው ያቀፉ ክልሎች ናቸው። እነዚህ አራት ክልሎች ደግሞ በግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ በመሆናቸው ለፋብሪካ አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውንም ግብዓት ከእነዚህ አራት ክልሎች ማግኘት የሚቻል በመሆኑ ከተማዋ የኢንዱስትሪ ማዕከል አድርጓታል።

በተለይም ነጻ የንግድ ቀጣና መኖሩ በራሱ ኢንቨስትመንቱን ለማበረታታትና ለመሳብ ትልቅ አቅም እንደሆነ ያስረዳሉ። ነጻ የንግድ ቀጣናው ድሬዳዋ ላይ በመሆኑ ወደፊት ባለሃብቱ ያለማንም ቀስቃሽ ወደ ድሬዳዋ በመምጣት ማልማት የሚችልበት ዕድል እንደሚኖረው፤ ይህም ነጻ የንግድ ቀጣናው የውጭ ባለሃብቶችን በመሳብ ለውጭ ኢንቨስትመንት ትልቅ አቅም እንደሚሆን ነው ያመለከቱት።

‹‹ነጻ የንግድ ቀጣናው ምንም እንኳን በፌዴራል መንግሥት የሚተዳደር ቢሆንም ለከተማ ዕድገት ትልቅ ድርሻ አለው ያሉት›› አቶ አበራ፤ ነጻ የንግድ ቀጠናን ጨምሮ ከተማ አስተዳደሩ የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ፈቃድ በከተማ አስተዳደሩ በሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ መንደር ውስጥ ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ሲሆን፤ ለውጭ ባለሃብቶች ፈቃድ የሚሰጠው የፌዴራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደእሳቸው ማብራሪያ፤ ድሬዳዋ ከተማ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነች ከተማ በመሆኗ በከተማዋ በርካታ ፋብሪካዎች ተከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ነው። ሶስት ሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ጨምሮ የውሃ ፋብሪካ፣ ዘይት ፋብሪካ፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ ሳሙናና ሌሎች ፋብሪካዎች በሥራ ላይ ናቸው። እነዚህ ፋብሪካዎችም ምንም አይነት የገበያ ችግር የሌለባቸው ሲሆኑ ይህም ማለት የድሬዳዋ ሕዝብ ቀደም ሲል ጀምሮ የኢንዱስትሪ ምርቶችን መጠቀም የጀመረ በመሆኑና አሁንም ድረስ በስፋት እየተጠቀመ በመሆኑ በከተማዋ በርካታ ፋብሪካዎች ይገኛሉ።

በቅርቡም ድሬዳዋ ከተማ ካሏት የኢንቨስትመንት አማራጮች መካከል አንዱና ትልቁ በሆነው የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማምረቻ ተመርቆ ወደ ሥራ ገብቷል። ማምረቻው በሰዓት ከ220 ቶን በላይ የኮንስትራክሽን ግብቶችን የማምረት አቅም ያለው ነው። ፋብሪካው በአካባቢው ለሚኖሩ ወጣቶች የሥራ እድል በመፍጠር ትልቅ ድርሻ ያለው ይኖረዋል። በተጨማሪም የአካባቢውን ማኅበረሰብ የኤሌክትሪክ ኃይልና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል። ይህም ከተማ አስተዳደሩ ለባለሃብቶች አስፈላጊውንና የተቀላጠፈ ምላሽ መስጠት በመቻሉ የተመዘገበ ውጤት እንደሆነ ነው አቶ አበራ ያመላከቱት።

እንደቡድን መሪው ማብራሪያ፤ ፋብሪካው በመጀመሪያው ምዕራፍ የምርት ሒደት 50 ለሚደርሱ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር ችሏል። በቀጣይም ፋብሪካው በሙሉ አቅም ወደ ምርት ሲሸጋገር ለተጨማሪ ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥር ይሆናል። ፋብሪካው የማምረት አቅሙ ከፍተኛ የሆነ ዘመናዊ ማሽኖችን የሚጠቀምና በርካታ የግብአት አማራጮችን ከጥራት ጋር የሚያቀርብ ድርጅት በመሆኑ ከድሬዳዋ አልፎ የአጎራባች ከተሞችና ክልሎችን የምርት ፍላጎት ጭምር ማሟላት የሚያስችል ነው።

‹‹የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ለኢንቨስትመንት ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ በመሆኑ በዘርፉ የጎላ ችግር አላጋጠመም›› የሚሉት አቶ አበራ፤ በቅርቡም የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ማምረት የሚችል ፋብሪካ ተመርቆ ወደ ሥራ መግባቱን ይገልፃሉ። አክለውም ‹‹ማንኛውም ሰው ድሬዳዋ ከተማን ቢጎበኛት ያተርፋል እንጂ አይከስርም። በተለይም የአገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች ወደ በረሃዋ ንግስት ድሬዳዋ ከተማ ቢመጡና መዋለንዋያቸውን ቢያፈሱባት በብዙ ያተርፋሉ›› በማለት ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።



## ጎሜ

# እውን እኛ የዓድዋ ልጆች ነን?

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያውያን አንድነት መለያቸው፤ ማሸነፍ ታሪካቸው ነው። ኢትዮጵያውያን ሲተባበሩ የማይደረምሱት ተራራ፤ የማያሸንፉት ጠላት፤ የማይወጡት አቀበት አይኖርም። ኢትዮጵያ ነጻነቷን አስከብራና የጥቁር ሕዝቦች መኪታ ሆና የዘለቀችው በሕዝቦቿ ትብብርና አንድነት ነው።

ትላንት ኢትዮጵያውያን አድዋ ላይ ቅኝ ገዢዎችን አሳፍረው መልሰዋል። በወቅቱ በመሪው አጼ ሚኒሊክና በተለያዩ ሀገረ ገዢዎች መካከል አለመግባባትና ቅራኔ ቢኖርም ሁሉም ነገር ከሀገር በታች ነውና ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው ወራሪውን የጣሊያን ጦር በአንድነት ድል ነስተዋል። በዚህም ኢትዮጵያን ከፍ አድርገዋል፤ ከዛም አልፎ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆነዋል። አንድት ኃይልም እንደሆነ ለቀሪው ዓለም የማይፋቅ ታሪክ ጽፈዋል።

በአጼ ሚኒሊክና በተለያዩ ገዢዎች መካከል ያለውን ልዩነት ተጠቅሞ ኢትዮጵያን ለመውረር የተነሳው የፋሺሽት ኃይል በኢትዮጵያን የተባበረ ክንድ ተደቁሶ ወደ መጣበት ከመመለሱም ባሻገር ኢትዮጵያውያን በውስጣቸው ልዩነት ቢኖርም ኢትዮጵያን ለማዋረድና ለመበታተን ለሚመጣ ኃይል ክፍተት እንደማይሰጡ ትምህርት ሆኗል።

የአድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተመው በንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክና በእቴጌ ጣይቱ አመራር ስር በአንድ ጥላ ተሰባስበው ባደረጉት ተጋድሎ የተመዘገበ ታሪካዊ ክስተት ነው። በአጠቃላይ አድዋ ከኢትዮጵያ አልፎ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ነው።

ሆኖም እኛ የአሁን ትውልዶች ድሉን የምንረዳው በዛ ልክ ነው ወይ የሚለው መጠየቅ ያለበት ጉዳይ ነው። እኔ እንደታዘብኩት ግን አድዋን የተረዳነው አይመስለኝም። ወይንም አንዳንድ ፖለቲከኞች ሆን ብለው ከጊዜያዊ ጥቅም ከማሰብ ድሉን ወደ ብሄርና ጎሳ አውርደው ለማሳነስ ሲጥሩ ታዝቤያለሁ። ይህንኑ ተከትሎም እንደፋሽን ይህንን ግዙፍ ታሪክ መንደር ውስጥ ለመወሸቅ የሚደረግ መውተርተር ጎልቶ ይታያል።

የአፍሪካን ድል ከጥቁር ሕዝቦችና ከአፍሪካ ድልነት አውርደን ወደ ብሄርና ሰፈር ለማሳነስ የምናደርገው ግብግብ እውን እኛ አድዋ መንፈስ ገብቶናል ወይ የሚያስብል ነው።

ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነው የመከሩበትና በጋራ ሆነው ልዩነታቸውን ሁሉ በመተው በመካከላቸው ቅሬታ ያለባቸው ሁሉ "ይቅር ለእግዚአብሄር" ተባብለው በአንድነት በመትመም በግማሽ ቀን ወራሪውን ኃይል ድባቅ የመቱበት ድል ነው። ታዲያ እኛስ ከዚህ ድል ምን እንማራለን።

የዛሬዎቹ ትውልዶች ከመተባበር ይልቅ መከፋፈልን፤ ከአንድነት ይልቅ ልየነትን፤ በጋራ ከመቆም ይልቅ መነጣጠልን አጥብቀን እንወዳለን። በዚህ ደግሞ ድል እንደማይገኝ ከአድዋ በላይ ምስክር የለም።

ጦርነቱን ለማስተባበር፣ ወረኢሉ ለመክተትና ከመላው ኢትዮጵያ ሰራዊቱ አድዋ ላይ እስኪገኝ በጥቅሉ አስር ወራትን መፍጀቱን የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። በመካከል ልዩነት ቢኖር፣ ንጉሰ ነገስት አፄ ሚኒሊክ የጠሩት ክተት ላይ መተማመን ቢጠፋና በአንድ ኢትዮጵያ መፅናት የጋራ ዓላማ ባይኖር ኖሮ አድዋን የሚያክል ግዙፍ ታሪክ ማስመዘግብ የሚታሰብ አልነበረም። ዛሬ ታዲያ በዚህ መልኩ ልዩነት ላይ አተኩረን ሀገራችንን አሸናፊ ማድረግ የምንችለው ? እንዴት ነው የእኛን ማደግ ማይፈልጉ የውጪ ጠላቶችን መርታት የምንችለው? እንዴት ነው ሊከፋፍሉንና ሊነጣጥሉን ሰርክ የሚሰሩ አካላትን ማሳፈር የምንችለው ?

የዛሬው ትውልድ መሪውን ምን ያህል ያዳምጣል?፤ በጎደለ ለመሙላት ራሱን ምን ያህል አዘጋጅቷል?፤ እሱ ወድቆ ወንድሙ እንዲያሸንፍ ምን ያህል ጨብጧል ? የተሰጠውንስ አደራ ምን ያህል ይጠብቃል ? ከስልጣን ይልቅ ሀገራችንን ምን ያህል እናስበልጣለን የሚለውን ከአድዋ ታሪክ አንጻር መመልከቱ በቂ ነው።

> በአድዋ ያ ታላቅ ድል የተመዘገበው በኢትዮጵ ያውያን መካከል ቀደም ሲል ምንም አይነት ልዩነቶች ስለሌሉ የሆነ አይደለም። ጠላት ሲመጣ ግን ኢትዮጵያውያኑ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው ለሀገራቸው ሉአላዊነት፣ ለነጻነት ያሳዩት እጅግ በጣም የሚደንቅ አንድነትና ቆራጥነት ለድል አብቅቷቸዋል

ንጉሰ ነገስቱ ለአስር ወራት ግንባር ላይ ሲቆዩ ራስ ዳርጌ የኢትዮጵያን መንግስት ሲመሩ እንደነበር፤ ይህም አንድ የጋራ አገርና ሕብረት እንደነበር ትልቅ ምሳሌ የሚወሰድ ነው። አጼ ሚኒሊክ ስልጣናቸው ሳያሳሳቸው ለራስ ዳርጌ አሳልፈው ሰጥዋል፤ ራስ ዳርጌም ስልጣን ሳያጓጓቸው አደራቸውን ጠብቀው ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።

አድዋ የአሸናፊነት ብቻ ሳይሆን የርህራሄም መገለጫ ነው። የሰው ልጅ ክብር የተገለጠበት ነው። ጣሊያኖች ብዙ ጀነራሎች፣ የጦር መሪዎችና ወታደሮች ሞተውባቸው ጦርነቱን ሲያሸነፉ ጭፈራና የድል ፈንጠዝያ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አልነበረም። እቴጌ ጣይቱ "የሞተው የሰው ልጅ ነው፤ ምንም ጭፈራ አያስፈልግም" በሚል አስከሬናቸው ፍትሃት ተደርጎለት እንዲቀበር አድርገዋል።

እኛስ ምን ያህል ይቅር ባዮች ነን ? ምን ያህል ሰብአዊነት ይሰማናል ? ወይስ የራሳችንን ወገን ዘቅዝቀን ምንሰቅል፤ የምናፈናቅል፤ የምንገድል፤ ሰዎች ሆነን ነው የምንቀጥለው። እስኪ እራሳችንን መለስ ብለን እንይ።

በአድዋ ዙሪያ የተጻፉ የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት፤ ‹እምቢ ለነፃነቴና ለሀገሬ ክብር› ብሎ ወደ ፍልሚያው የገባው ኢትዮጵያዊ ለእግሩ ጫማ አልነበረውም፤ ጥሻና ገደሉን በባዶ እግሩ በመውጣትና በመውረድ ነው የተዋጋው።

በእጁ የያዘው መሣሪያም የጠላትን ጦር ይመክታል ብሎ የሚገመትም አልነበረም። ኢትዮጵያውያን ኋላቀር የሚባለውን መሣሪያ ሊያውም በበቂ ሁኔታ ሳያገኙ፣ ጦርና ጋሻ ይዘው፣ ታላቅ ወኔ ተላብሰው፣ የንጉሰ ነገስት ዳግማዊ አጼ ምኒሊክና የእቴጌ ጣይቱን የጦርነት ስልት ተጠቅመው በመዋጋት ጠላትን መግቢያና መውጫ አሳጥተው ነው አድዋን ያህል ታላቅ ድል መቀዳጀት ችለዋል።

የዛሬውስ ትውልድ ቅድሚያ የሚሰጠው ለምቾቱ ነው ወይስ ለሀገሩ ? ለሀገሬ ልስጥ ነው ወይስ ሀገሬ ትስጠኝ የሚለው ? ይህ እያንዳንዳችንን የሚመለከትና ምላሹም ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ነው።

የዓድዋ ድል የትብብርንና የአንድነትን ውጤታማነት እንዲሁም ለነፃነት መስዋዕትነት መክፈል ታላቅ ክብር እንደሆነ ያሳየ፣ የነጮች የበላይነት ማክተም እንደሚችልም የጠቆመና መንገድ የከፈተ አንፀባራቂ ክስተትም ነው። ይህን ክብርና መንገድ በጀግንነትና በመስዋዕትነት በታጀበ ተግባር ያሳዩትና የመሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ የጭቁኖች መመኪያ መሆናቸውን አስመስክረዋል።

ከዚህስ አንጻር የአሁኑ ትውልድ ከራሱ አልፎ ለሌሎች ጥቁር ሕዝቦች ምን ያህል መመኪያ ሆኗል ? እራሱን ነጻ አውጥቶ ሌሎችን ነጻ ለማውጣት ምን ያህል ዝግጁ ነው ? በተለይም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተፈጠረውን የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ተገንዝቦ እራሱን እና ሀገሩን ምን ያህል እየተከላከለ ነው ? በየቀኑ በሶሻል ሚዲያ አማካይነት እየተሰራጩ ከሚገኙ ትውልድ አምካኝና ሀገር አጥፊ መልዕክቶች እራሱን ሀገሩን ምን ያህል እየጠበቀ ነው ?

የዓድዋ ድል ፋይዳዎች በርካታ ናቸው። የመጀመሪያው ኢትዮጵያን ከወራሪ ኃይል ጠብቆ ማቆየት ቢሆንም በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀች በአጠቃላይ ኃያል የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠርና መገንባት ነበር። ይህ የተቀደሰ ዓላማ ምን ያህል ተሳክቷል ?

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነፃነት፣ ክብርና አንድነት ሲሉ በዓድዋና በሌሎች ስፍራዎች ለማመን የሚከብዱ ከባድ ተጋድሎዎችን አድርገው ነፃ አገር ለ‹‹ተተኪው ትውልድ›› ቢያስረክቡም፣ ተተኪው ትውልድ ከአንድት ይልቅ ልዩነት በመምረጥ እርስ በራሱ ሲገዳደል ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህ አስከፊ ሁኔታም ዛሬ ድረስ ቀጥሏል።

ኢትዮጵያ በዘር፣ በኃይማኖትና በአመለካከት ሳይከፋፈሉ ዓድዋ ላይ ጠላትን ድል ያደረጉ ልጆች እናት መሆኗን ማሰብና ከዓድዋ ድል በኋላ ባፈራቻቸው ‹‹ልጆቿ›› ምክንያት በአስከፊ የዘር ፖለቲካ ስትታመስ መመልከት እጅግ አሳዛኝና አስገራሚ ተቃርኖ ነው። ይህ ውድቀት ደግሞ በእውነት እኛ የአድዋ ልጆች ነን የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል።

አድዋ የአንድነትና ተባብሮ የመስራት ውጤት ነው። በወቅቱ ኢትዮጵያም ልክ እንደሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች በኃይማኖት፣ በዘርና በቋንቋ የተለያዩ ሕዝቦች ያሉባት ሀገር ነበረች" የሚሉት ምሁሩ፣ ኢትዮጵያውያን በዘር፣ በኃይማኖት፣ በቋንቋ ቢለያዩም፣ ከነበረው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የተነሳ፣ ለነጻነታቸውና ለሀገራቸው ባላቸው ቀናኢነት ሁሉም በአንድነት ተሰልፈው የሀገርን ሉአላዊነት ሊዳፈር የመጣውን ጠላት በመመከት ማሸነፍ መቻላቸውን ያመለክታሉ። ያ የጣሊያን ጦር ዘመናዊ በሆነ አደረጃጀት የተዋቀረ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያውያን፣ በመሪዎችና በጦር አመራሮች መካከል የነበረውን አንድነትና በሕዝቦች መካከል የታየውን ጠንካራ የተሳሰረ የአንድነት መንፈስ ፈጽሞ ሊሰብረው እንዳልቻለ ያስረዳሉ።

በአድዋ ያ ታላቅ ድል የተመዘገበው በኢትዮጵ ያውያን መካከል ቀደም ሲል ምንም አይነት ልዩነቶች ስለሌሉ የሆነ አይደለም። ጠላት ሲመጣ ግን ኢትዮጵያውያኑ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው ለሀገራቸው ሉአላዊነት፣ ለነጻነት ያሳዩት እጅግ በጣም የሚደንቅ አንድነትና ቆራጥነት ለድል አብቅቷቸዋል። ለድሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ባለው የኀብረተሰብ ክፍል መካከል የታየው አንድነት፣ የአመራር ብቃት፣ ችሎታና ጠንካራ የሆነ ቁርጠኝነት መሆኑን ይጠቅሳሉ። የኢትዮጵያ ሉዕላዊነት የተጠበቀው ኢትዮጵያውያን ባሳዩት አንድነትና የዓላማ ጽናት ነው ማለት ይቻላል።

አድዋ ላይ የተገኘው ለጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት የሆነው ድል በሁሉም ነገር አንድ ስለሆንን የተገኘ አይደለም፤ ሆኖም ግን ልዩነቶችን ወደ አንድነት በማምጣት ተባብሮ መሥራት ለድል እንደሚያበቃ መመልከት ችለናል ይላሉ። ከአድዋ ድል የምናገኘው ትልቅ ትምህርት አንድነታችንን ብንጠብቅ ልክ እንደ አድዋ ሉዕላዊነታችንን የሚዳፈር አንዳች ጠላት በሚመጣበት ጊዜ ሉአላዊነታችን አስጠብቀን ለትውልድ ማስተላለፍ እንደሚቻል ያሳየ ነው።

ከጣሊያኖች ስትራቴጂ አንደኛው የኢትዮጵያውያንን አንድነት ሊቦረቡር በሚችል መልኩ የተለያዩ ሀገር ገዢዎችን በጥቅማጥቅም ማማለል አንዱ እንደነበር ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያኑ በሀገር ጉዳይ ምንም አይነት ድርድር አያውቁምና ይህን ስትራቴጂም አክሽፈዋል።

አባቶቻችን በጣም በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው ታሪክ ሠርተው የአድዋን ድል አስመዝግበዋል ያሉት ምሁሩ፣ በሚመች ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በጣም በማይመች ሁኔታ ውስጥም ሆነን ለመጪው ትውልድ ሊተርፍ የሚችል ታሪክ መሥራት አለብን ፡

ዛሬም የአድዋን ድል መሰል የጀግንነት ስራ ልንሰራባቸው የሚገቡ በርካታ የቤት ስራዎች ያሉን ሕዝቦች ነን። አገራችን እንደ አደዋው ዘመን በቀጥታ ቅኝ ሊገዟት ባይመጡም በእጅ አዙር ሊያንበረክኳት የእነሱ ተላላኪ የሆነ መንግስት ሾመው እንደፈለጉ ሊፈልጧት ሊቆርጧት የሚቋምጡ በርካታ የዓለም አገራት መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ስለዚህም እኛ ልክ እንደ አድዋ ጀግኖች የውጭ ወራሪዎችን እና ተንኮለኞችን ሴራ ለማክሸፍ ምን ያህል ዝግጁዎች ነን ? የሚለው መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ጥበብ ቤቷን ሠራች

ሙሉጌታ ብርሃኑ

የጥበብ ቤት እንደ ድንጋይና እንጨት የሚፈርስ፤ የሚናድ አይደለም። ጥበብ ቤቷን ሥትሰራ ቢችል አናጢ ባይችል መዶሻና ሚስማር ላቀበለ ሁሉ ዋጋዋ ትልቅ ነው። ባሳለፍነው ዓርብ ወርሃ የካቲት አሀዱ ብሎ በጀመረበት ቀን በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ውስጥ ትልቅ እንድምታ ያላቸው ሁለት አበይት ጉዳዮች ተከናውነው አልፈዋል። እነዚህ ሁለት ነገሮች በዕለቱ አሊያም በዓመቱ ብቻም ሳይሆን በዘመን ሁሉ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

አንደኛውን ጉዳይ ስናነሳ፤ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ለመሥራት ስለታቀደው የ"ፈረጃ" ፊልም ይሆናል። በዕውቁ ተዋናይ ሔኖክ ወንድሙ የተጸነሰው የዚህ የሕዝብ ፊልም ሀሳብ ከአንድ ደረጃ ላይ ደርሷልና የት ደርሶ ይሆን በሚል የፊልሙ ዋና አዘጋጅ በሆነው በዚሁ ተዋናይና በሌሎችም የፊልም ባለሙያዎች የደረሰበትን ደረጃ ለሕዝቡ አሰሙልን ሲሉ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተውበታል። ከዚሁ መግለጫ ጋር የዚህን ታሪካዊ ፊልም ውጫዊ ዳሰሳ በቀጣዩ የሳምንት አምዳችን እንቃኛለን። ዛሬን በሁለተኛው ርዕሰ ጉዳይ መሰንበቻ እናድርግ።

ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ደራሲያኑ መንደር ያመራል። በአንጋፋው የደራሲያን ማኅበር ቤት ውስጥ ብሩህ ሰማይ ከብርሃን ጸዳል ጋር ታይታለች። ሁለተኛው የዕለተ ዓርብ ጦማር ሲፈታ መልካም ብስራት ለደራሲያኑ እንዲሁም ለማህበሩ ይለናል። ባደጉት ሀገራት ብቻም ሳይሆን በብዙዎቹ ዘንድ አስከብሮና አንደላቆ የሚያኖረው የደራሲያኑ ዓለም ለኛ ሀገር ግን ያለመታደል ሆኖ የችግር መሰንቆ ነው። ማኅበሩም በችንካር ቆሞ ስለመከረሙ ለማንም ነጋሪ አያሻውም። የ60 ዓመታት የዕድሜ ባለጸጋ ሆኖ ሳለ፤ ዛሬም ግን በሁለት እግሩ ቆሞ ለመሔድ ሳይችል ቀርቶ እንደ ሕጻን ልጅ በእጁ ሲድህ ማየት አጥንት የሚሰብር ነው።

ብስራቱም ይህ ነው፤ ወድቆ ላለመሞት ከሚፍጨረጨርበት የሞት ሽረት ትግል ወጥቶ እራሱንም ችሎ ለሌላውም መትረፍ የሚችልበትን ትልቁን የ3 ሺህ ካሬ ሜትር የሕንጻ ግንባታ ለማድረግ የተነሳበትን የመጀመሪያውን እውን እርምጃ ለማሳየት ቻለ። በየካቲት 1 ቀን፤ ከአንድ የግንባታ ድርጅት ጋር በመፈራረም ጉዞውን አብስሯል።

ጥበብ ቤቷን ሠራች ማለታችን በምክንያት ነው። ስንልም ደግሞ በአይን የሚታየውን ቁሳዊውን ቤት ብቻም ለማለት አይደለም። ከዚህ ቁሳዊ ቤት በስተጀርባ የሚመጣ ጥበባዊ ትንሳኤም በመኖሩ ነው። እንደሚታወቀው የደራሲያን ማኅበሩ እጅግ እግሩ ጠፍሮ ለራሱም ለሌላውም እንዳይሆን ያደረገው ትልቁ ነገር ገንዘብ ነው። ገንዘብ የሚለውን ችንካር በዚህ ነቅሎ ለማውጣት ያስችለዋል። ከእግሩ እሾህ ለገባ፤ መጀመሪያ የሚያስፈልገው ነገር መርፌ አሊያም እሾህ ነው። ማኅበሩ የዚህ ሕንጻ ባለቤት ከሆነ በኋላ ያለበትን መርዛማ እሾህ ነቅሎ በማውጣት በደንብ ወደፊት ለመራመድ የሚያስፈልገው ብልሀት ብቻ ነው።

በደራሲያን ቤት ውስጥ ደራሲያን አሉ፤ ብዕራቸው የነተበ ትጉህ ብዕረኞች ድሮም ዛሬም ድረስ፤ ከዚሁ ችግር የተነሳ ቤቱ የነዚህን ደራሲያን ሥራዎች በባለቤትነት ለመምራትና ለሚያስፈልጋቸው ወሳኝ ነገሮች መድረስ ሳይችል ቀርቷል። እንደብዙ ሀገራት ተሞክሮ የደራሲያኑ ማኅበር አባላት ሥራዎችን መሥራት እስከቻሉ ድረስ የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልም። የኛ ሀገርስ ለምን? ብለን እንዳንል፤ እንኳንስ ለማህበሩ አባላትና ለራሱም ያጣ የነጣ ሆኖ ጉስቁልቁል ያለ ፊቱ ነው የሚታየን። በዚህ ሁሉ ዘመናት አንጀቱ ተበጥሶ ላለመውደቁም፤ ከአባላቱ ከሚሰበሰብ ጥቂት ገንዘብና ከአንዳንድ የውጭ ድጋፎች ነው። እንጂማ፤ የሀገር ባለውለታ ሆኖ ሳለ እንደመረሳቱ ቢሆንማ ኖሮ፤ ለማስታወሻነት የምትሆን ጨርቁን እንኳን ባላየን ነበር። ምስጋና ለእነዚህ የጥበብ ልጆች ይግባና ለአይን በማይታይ ዱር ገደሉ ሁሉ ሲታገሉና በጫንቃቸው ተሸክመው ወንዙን እያሻገሩ ዛሬ ላይ እንዲደርስ ሆኗል።

የተባለው ቤት ሲሰራ፤ ጥበብም የራሷን ቤት ከውስጡ ትሰራለች። ስንቱን ከሞት ሊቀሰቅስ የሚችለውን የጥበብ ሥራዎቻቸውን፤ በገንዘብ እጦት ምክንያት እንደታቀፉት አብረው ለሚያልፉት አባላቱ ትልቅ የምስራች በር ነው። ምናልባትም ከዚያን ወዲያ የሚጨነቁት ምንና እንዴት ልሥራ በሚል ይሆናል፤ ምክንያቱም እንዳይንቀሳቀሱ ከሆዳቸው ሰትሮ የያዛቸው የገንዘብ ችንካር በማህበሩ ተነቅሏልና።

እንደ አንድ ደራሲ ብቻም ሳይሆን እንደተቋሙ የሚኖረው ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴም ከወትሮው ለወጥና ለየት ያለ ይሆናል። ታዲያ፤ ከማኅበሩ ቡስካ በስተጀርባ፤ ቤቷን የሠራችው ጥበብ ናት ብንል ዋሾ ሊያስብለን የሚችል ምንስ አለና።

ስለ ቤቱና ዕለቱ ደግሞ ጥቂት እንበል። ለዚህ ዕለት ስኬት ለመድረስ የማህበሩ አባላት የከፈሉት ዋጋና የላይ ታች ውጣውረድ ቀላል የሚባል አነበረም። በተለይ ደግሞ ጉዳዩን ከግብ ለማድረስ ወዲያና ወዲህ ሲሉ በአንድ ወቅት የመኪና አደጋ ሁሉ ደርሶባቸው የነበሩት የማኅበሩ ሊቀመንበር የዝና ወርቁ ከብዙዎች ምስጋና ተችሯቸዋል። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር እስትንፋሱ ሳይቋረጥ ዛሬም ድረስ መኖሩ በእንደነዚህ አይነቱ የግል መስዋዕትነትና እንደርሷ ባሉ መንፈሰ ብሩሃን ነው። በእያንዳንዱ ስድሳ ዓመታት መካከል፤ እሾሃማውን ቀንበር ተሸክመው በቅብብሎሽ ያመጡ እጅግ በርካታ ናቸው።

ለማኅበሩ ብቻም ሳይሆን፤ እንደ ሀገር ለሀገር ባለውለታ ሆነው፤ የማኅበሩ አንድ አካል የነበሩ ብዙ ደራሲያን የሞቱት በስጋዊ ብቻም ሳይሆን በምስጋና እጦትም ጭምር ነው።

"ምስጋና ትልቅ ነገር ነው። አንጥንትና መንፈስንም ያለመልማል። ከምንም በላይ፤ የቤት ግንባታውን ለማከናወን እኔ አለሁ ሲል የመጣውን የግንባታ ድርጅትም ሊመሰገን ይገባል። የሚያገኘውን ትርፍ ሳያሰላ በመልካምነት በመምጣቱ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነውን የመረዳዳት ባሕል አሳይቶናል። በዚህ ሥራ ውስጥ፤ የኛ የደራሲያን ማኅበርም ሆነ ድርጅቱ፤ ሁለቱም የቆሙት በአንድ ዓላማ በመሆኑ ደስ ብሎኛል" ሲሉ የዝና ወርቁ ንግግራቸውን አደረጉ።

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ከተመሰረተበት ዕለት አንስቶ በተጓዘባቸው 60 የድክርትና የመፍገምገም ዓመታት ውስጥ በጥበብ ወጭቱ እውቀትን፤ በማድጋው የመንፈስን መና እየሞላ ኢትዮጵያን ገንብቷል፤ የገነቡትንም ወልዶ አሳድጓል። በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ብቻም ሳይሆን በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያኖረው የብርሃን ላንባ፤ በነበልባሉ ውስጥ መልክና ታሪኩን ያሳያል።

በሀገራችን በተካሄዱ የፖለቲካ ለውጥና ሥርዓቶች ውስጥ ከማንም በላይ ደራሲያኑ፤ ከፊተኛው ረድፍ ላይ ነበሩ። በብዕራቸው ሳይቆሙ፤ አሳልፈው ደረታቸውን ለጥይት የሰጡ ጥቂት አይደሉም። ኢትዮጵያን የመቀየርና ከሰቆቃው ድኅነት የማውጣት ሕልማቸው ታላቅ ነበር። ሁሉም የማኅበሩ አምሳል፤ እጅና እግር ነበሩ። እነዚህ የንጋት ከዋክብት በችግር ማቀው፤ እንደ ጠዋት ጤዛ ሲረግፉ ነገር ግን ያ "ሀገር ማለት ሰው ነው" ነው የተባለው አምሳለ ሀገሩ ሰው ግን ሳይደርስላቸው፤ ለስጋም ሆነ ለመንፈስ የሚሆን አዱኛ ሳይሰጣቸው አምልጠውት ሄደዋል።

ወደኋላ ተመልሰን፤ የብዙ ደራሲያንን ሕይወት ለማየት ብንሞክር የምናገኘው አንድ አይነት ሕይወት፤ አንድ አይነት መረሳትና መገፋት ነው። ባለውለታ ሲታለፍ በዝምታ፤ ብርቃችን አይደለም። ይህ ጥቁር ጥላሸት፤ ዛሬም ድረስ ለምልክት በደራሲያን ማኅበር ፊት ላይ እንደማዲያት ሆኖ ይታያል።

የነገሩን ጫፍ ወዲህ ስንመዘው፤ ይህ ማኅበር በአሁኑ ሰዓት የጀመረው የሕንጻ ግንባታ፤ ያለፈ እንባውን ባይጠርግለትም በተስፋ እየተጽናና ወደ አዲስ ማንነት እንዲገባ ያደርገዋል። ቀደም ሲል ከመንግሥት ያገኛት የ3 ሺህ ካሬ ሜትር የመሬት ስጦታ ምናልባትም ለትውልድ ሁሉ የሚሆን፤ የዘለዓለም ሕይወቱ የሚተከልበት ይሆናል። ማኅበሩ ከአፈሩ፤ ጥበብ ደግሞ ከአየሩ ላይ ቤታቸውን ይሠሩበታል።

ይህን ለመሥራት ታዲያ ማኅበሩ አሁንም የገንዘብ ችግር አለበት፤ ሳንቲም እንኳን ወድቃ ቅጭል የምትለው ከመንደሩ ርቃ ነው። በአንድ ወቅት የዚሁ ማኅበር አባል ከሆነ ሰው ጋር ተገናኝተን ስናወራ ያለኝ ነገር ትዝ አለኝ። ድንገት በጨዋታ መሀል ስለ አንድ ጉዳይ ልጠይቀው ፈለኩና ነገርየውን ማኅበሩ ያከናውነው እንደሆን በማለት ብጠይቀው ጊዜ "አይ...ወዳጄ እኛ ለራሳችን ጡረተኞች ነን" ሲል ቁጭት በታከለበት ስሜት ውስጥ ሆኖ መለሰልኝ። በርግጥም አላጋነነውም፤ የ60 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ የሆነ ማኅበር ምንም የገቢ ምንጭ ሳይኖረው ከዚህም ከዚያም እያለ ለመሰንበት ታህል ብቻ ሲኖር ቆይቷል። በዚህ መልኩ ለቆየው የደራሲያን ማኅበር የሕንጻ ግንባታውን ለማካሄድ ምናልባትም ተአምር ያስፈልገው ነበር፤ ያውም የ40 ሚሊየን ብር ተአምር። ለዚህ ገንዘብ፤ አለሁልህ በማለት ከጎኑ የሚቆምለትና የሚደግፈው አካል የግድ ነበር። ለዚህ በጎነትም ዲቢ የተገጣጣሚ ቤቶች እራሱን አቅርቧል። በተገጣጣሚ ቤቶች፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባለመብት የሆነው የዲቢ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ የሆኑት፤ መሀንዲስ ብርሃኑ ካሳ የካቲት አንድ በነበረው ዝግጅት ላይ ተገኝተው ተፈራርመዋል።

ይህ በሁለቱ አካላት መካከል የነበረው ስምምነት እከክልኝ ልከክልህ የሚመስል ቢሆንም፤ ነገር ግን ከመጠቃቀም ይልቅ መጥቀምን መሰረት ያደረገ የበጎነት ነጸብራቅ ነው። ጥበብ ቤቷን ለመሥራት የግድ ካላት፤ በየትኛውም አስቸጋሪ ዘመናት መሃከል ሰው አጥታ አታውቅምና ዛሬም የሆነው ይሄው ነው። ያን ያህሉን ገንዘብ ቆጥሮ ለማሰራት ለማይችለው የደራሲያን ማኅበር፤ ድርጅቱ በራሱ ወጪ ለመገንባት ተስማምቷል። ታዲያ በምትኩ፤ ከግንባታው መልስ ለአምስት ዓመታት ያህል በጊዜያዊነት ተረክቦ በኪራይና በመሰል አገልግሎቶች ወጪውን ለማካካስ ይሞክራል። በእኚህ 5 ዓመታት ያወጣውን ይመልስለት ይሆን? ብንል፤ ለምላሹ በሂሳባዊ ቀመር ብዙ ለመጠበብ አያሻንም፤ የዝና ወርቁ እንዳሉትም "በእርግጠኝነት አይመልስለትም"። ይህንኑ ጥያቄ ለግንባታ ድርጅቱ ባለቤት፤ ለብርሃኑ ካሳ በማቅረብ፤ እንዴትስ ይህን ለማድረግ እንደፈለጉ በተጠየቁ ጊዜ እንዲህ ነበር ያሉት፤ "እኛ የምንሰራው ድንጋይ ነው፤ ደራሲያኑ ግን የሚሰሩት ሰውን ነው። እኛ ሁላችንም የእነዚህ ደራሲያን ውጤቶች ነን፤ ያሉትም የሞቱትም። ይህን ለመስራት ስወስን አተርፍበታለሁ በማለት አይደለም። ስራው እንደ ሀገር ምናልባትም ትንሽ ነገር ሊሆን ይችላል፤ እንደኛ ድርጅት ግን ለሀገራችን ባለውለታዎች መስራት በመቻላችን እድለኞች ነን። ትልቁ ታሪካችንም ነው። በእነዚያ አምስት ዓመታት፤ ምናልባትም ያወጣነውን ግማሽ ያህሉን ብቻ ይሆናል የምናገኘው፤ ግን በጣም ደስተኞች ነን። ለደራሲያን ማኅበር መስራት ማለት ለሀገር መስራት ማለት ነው።

በሚሠራው በዚህ የጥበብ መንደር ውስጥ ከቤቶቹ ከፊሉ ለመጽሐፍት መሸጫና አዳዲስ የሕትመትና የጥበብ ውጤቶች የሚሰፍሩበት ይሆናል። እንዲሁም የአባላቱ የጥበብ ሥራዎችም ከመጀመሪያው፤ ከሕትመትና ስርጭቱ ጀምሮ በኃላፊነት የደራሲያን ማኅበር የሚረከበው ስለመሆኑ የማኅበሩ ሊቀመንበር፤ አበረ አዳሙ አንስተውታል። ከበስተጀርባ ጥበብ ቤቷን ሠራች፤ ትሠራለች ስንል አንድም ለዚህ ነው። ከምንም ነገር በላይ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ጥበብ የምትፈልገው ሰውን ነው። ሌላው ቀርቶ የማኅበሩን የእውቅና ደረጃ ከፍ በማድረግ ጎልቶ እንዲወጣ ለማስቻል እንኳን ሰው የሚያስፈልግ ቢሆንም ግን የለም ለማለት ያስደፍራል።

በደራሲያን ማኅበር የታሪክ ማኅደር ውስጥ፤ እስከዛሬ ድረስ እንደ ግለሰብ በክብር አባላትነት የተመዘገቡ ብቸኛው ሰው፤ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ብቻ ናቸው። እንደ ተቋም ደግሞ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ጨምሮ፤ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ድርጅት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እና የብሔራዊ ቤተ መጽሃፍትና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ ይገኙበታል። እንደኛ ሀገር እምብዛም ስለማንጠቀምበት ነገሩ ቀላል ቢመስለንም፤ እንዲህ እንደ ደራሲያን ማኅበር ላሉት፤ እውቅ ተቋማትንና ዝነኛ ግለሰቦችን አስጠግቶ ከሥሩ ማድረግ ያለው ሚና ዳጎስ ያለ ነው።

"አንድ አሜሪካዊ ጠቢብ ባለጸጋ ነበር። ይህም ሰው በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ሊባል የሚችል ዘመናዊና ቅንጡ ቤት ለመስራት ፈለገና ዕቅድ ነድፎ፤ በቆንጆ ዲዛይን ሰርቶ አዘጋጀው። መሰረቱንም ጣለ። ከዚያም ሥራውን በንድፉ መሰረት ለመስራት እንደጀመረ ሕይወቱ አለፈ። ባለቤትየውም የባለ ራዕይውን ራዕይ ተሸክመው፤ ከውስጣቸው የሀዘን ማቅ ሳይለብሱ ሥራውን አስቀጠሉት። ቤቱም ተገነባና የታሰበው ተቋም እንደታሰበው ተሰራ። እናም ከተጠናቀቀ በኋላ፤ በመጨረሻው ቀን የዓለም መሪዎችና ታላላቅ ጋዜጠኞች የተገኙበት ዝግጅት ተደረገ። ጋዜጠኞቹም ወደ ሴትየዋ በመሄድ "እንዲያው ባለቤቶት በሕይወት ኖረው ይህን ቢያዩ እንዴት ደስተኛ በሆኑ ነበር፤ ለማንኛውም በመካከላችን ባለመገኘታቸው በጣም እናዝናለን! እና ምን ይሰማዎታል?' አሏቸው። ሴትየዋም ፈገግ በማለት እንዲህ ብለው መለሱ "የኔ ወንድም ተሳስተሃል፤ ባለቤቴ እኮ ይህንን አይቶና ጨርሶ ነው የሞተው፤ እንጂ ጀምሮ አይደለም የሞተው፤ ሲሉ መለሱለት" አሉ፤ የቀድሞው የማኅበሩ ሊቀመንበር፤ አንጋፋው አርቲስት ጌትነት እንየው፤ ከመጻሐፋቸው በቀነጨቧት ታሪክ። ጥበብም እንዲሁ ናት፤ ምነው ይህን አይተው በሞቱ ኖሮ አትልም። ዛሬ ለምትሠራው ቤት መሠረቱን የጣሉትና አስቀድመው ያዩት፤ እነዚያ የሔዱቱ ስለመሆናቸው ታውቃለችና ለዘነጋናቸውም ሁሉ የዋጋቸውን ትከፍላለች።



የዝና ወርቁ

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ስደተኛ ማን ነው?

**ዋሰልኝ አዩስ**

በተለምዶ የምንጠቀማቸው ብዙ ቃላት አሉ፤ ዳሩ ግን በሕጋዊ አገባባቸው ሲታዩ ደግሞ ትክክል ያልሆኑ (እንዲያውም ይባስ ብሎ ሕገ ወጥ የሆኑ) ናቸው። ከእነዚህም አንዱ ‹‹ስደተኛ›› የሚለው ቃል ነው። የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ባለፈው ሳምንት (ከጥር 28 እስከ 30) ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች በስደተኞች አዋጅና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና ሰጥቶ ነበር። ሥልጠናውን የሰጡት የተቋሙ ባለሙያዎች ገጠመኞቻቸውን ሲናገሩ፤ ብዙ ሰዎች ከስደተኝነት ጋር በተያያዘ ግንዛቤው የላቸውም። ሊያሳውቁ የሚገባቸው ጋዜጠኞች ራሱ አግባብ ባልሆነ መንገድ ሲጠቀሙ እና ተቋሙ ኃላፊነቱ ያልሆነውን ነገር ሁሉ ሲጠይቁ ይስተዋላል። ይህ የሆነው አዋጁን በሚገባ ካለማወቅ እና የቃላት አገባባቸውን ባለመገንዘብ ነው።

ወደ ልማዳዊ አገላለጾች እንመለስ። በልማዳዊ አገላለጽ ‹‹ስደተኛ›› የሚባለው ማንኛውም አካባቢውን ለቆ የሄደ ሰው ነው። ይባስ ብሎ በሀገሩ ውስጥ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሄደውንም ‹‹ስደተኛ›› ሲባል ይሰማል። አካባቢውን ለቆ የሄደው ሰውም ‹‹ተሰድጄ›› ሲል ይሰማል። ልክ አንዳንድ ሰዎች (በተለይም በገጠር አካባቢ) አካባቢያቸውን ‹‹ሀገሬ›› ብለው እንደሚጠሩት ማለት ነው። ራቅ ካለ አካባቢ የመጣን ሰው ‹‹ሀገርህ የት ነው?›› ብለው ይጠይቁታል። መላሹ ‹‹ሱዳን፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ....›› ብሎ አይደለም የሚመልስ። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ አንድ አካባቢ (የመጣበትን) ይናገራል። ይህ በልማዳዊ አገላለጽ ነው፤ ሕጋዊና አግባባዊ አገባቦችን ባለማወቅ ነው።

ልክ እንደዚህ ሁሉ፤ ስደተኛ የሚለውን ቃል ሕጋዊ ባልሆነ አገባቡ እንጠቀመዋለን። ይህ በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ችግር አይደለም። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በዚሁ ጉዳይ ባወጣው አንድ ሐተታ፤ ስደተኛ፣ ፍልሰተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ የሚሉትን ቃላት ሰዎች በተተካኪነት ሲጠቀሟቸው ይስተዋላል። ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚጠቀሟቸው በእንግሊዘኛ ቃላት ስለሆነ የተሰጣቸው ትርጓሜ ዓለም አቀፍ ይሆናል። ወደ አማርኛ ስናመጣው ግን ምናልባትም አንዳንዶቹ ላይ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። እስኪ የተሰጣቸውን ትርጓሜ እንመልከት።

ስደተኛ (refugee) ማለት በአንዲት ሀገር ለመኖር ሕጋዊ ዕውቅና ያገኘ ከሌላ ሀገር የመጣ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ከኤርትራ ወይም ሶማሊያ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ፣ የስደተኝነት ዕውቅና አግኝቶ በኢትዮጵያ የሚኖር ማለት ነው። ይህን ዕውቅና የሚያገኘው ከዜግነት ሀገሩ በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች ለመሰደድ የበቃ ሲሆን ነው። የሚሰደድበት ምክንያት ጦርነት፣ የዘር ወይም የሃይማኖት ጥቃት ሊሆን ይችላል። በአጭሩ ስደተኛ ማለት ጥገኝነት በጠየቀበት ሀገር ውስጥ ዕውቅና ያገኘ ማለት ነው።

ጥገኝነት ጠያቂ (asylum seeker) ማለት ደግሞ በድንበር ወይም ጠረፍ ላይ ሆኖ የስደተኝነት ዕውቅና ለማግኘት የሚጠይቅ ማለት ነው። የስደተኝነት ዕውቅና ለመስጠት ሥልጣን ላለው አካል አመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚጠባበቅ ማለት ነው።

ፍልሰተኛ (Migrant) ማለት ቃሉ እንደሚገልጸው ከሀገራቸው ፈልሰው ወደ ሌላ ሀገር መሄድ ማለት ነው። የአማርኛውም ሆነ የእንግሊዘኛው ቃል ሕጋዊ ትርጉም አልተሰጣቸውም። ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የላቸውም። እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ ተቋማት ግን ያውቋቸዋል። ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት (IOM) የሚባል የተባበሩት መንግሥታት ተቋም በዚሁ ጉዳይ ላይ የሚሠራ ነው። ፍልሰተኞች ላይ የሚሠራ ተቋም ቢሆንም ፍልሰተኞች (Migrants) ግን ዓለም አቀፋዊ ሕጋዊ ዕውቅና የላቸውም። ፍልሰተኞች በፈለጉ ጊዜ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ናቸው።

በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ምሳሌ ከወሰድን በሊቢያ በኩል አድርገው ወደ አውሮፓና ሌሎች ሀገራት የሚሄዱት የሀገራችን ዜጎች ማለት ነው። ፍልሰተኞች የሚሄዱት የተሻለ ኑሮ ወይም ትምህርት ፍለጋ ነው። በሀገራቸው ምቹ ኑሮ አላገኘንም በሚል ሠርቶ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው። እነዚህን ሰዎች በተለምዶ ‹‹ስደተኞች›› ስንላቸው ይሰማል። በሕጋዊ አግባብ ግን ስደተኞች ሳይሆኑ (ዕውቅና ስላላገኙ) ፍልሰተኞች ይባላሉ።

ተፈናቃይ (Internally displaced people) የሚባለው ደግሞ ቃሉ እንደሚገልጸው ከአካባቢው የተፈናቀለ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ከሀገራቸው አይወጡም። የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ እንደ ማሳያ ብንወስድ፤ ከአንድ የኢትዮጵያ አካባቢ በጦርነት ወይም በድርቅ፣ ወይም በሌላ ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌላ የኢትዮጵያ አካባቢ ተፈናቅለው የሄዱ ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እንደ ስደተኛ የማየት አጋጣሚ እንዳለ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ባለሙያዎች ገጠመኞቻቸውን ተናግረዋል። የተቋሙ ስያሜ ‹‹ስደተኞችና ተመላሾች›› ስለሚል ተፈናቃዮችን ‹‹መቼ ነው ወደ ቀያቸው የሚመለሱ?›› የሚል ጥያቄዎች ይቀርቡላቸዋል። የስደተኞችና ተመላሾች ጉዳይ ግን ዓለም አቀፍ ጉዳይ ነው፤ ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚያገናኝ ነው። በዚህ አጋጣሚ ተመላሾች ማለት በስደት ከቆዩበት አገር ወደ ትውልድ ወይም የዜግነት ሀገራቸው የሚመለሱ ማለት ነው።

የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ባለሙያዎች የዳሰሳ ጥናት መረጃ እንደሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ120 ሰዎች አንዱ ስደተኛ ነው። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ደግሞ ከ26 ሀገራት የተቀበለቻቸውን ስደተኞች ታስተናግዳለች።

በነገራችን ላይ ይህ የኢትዮጵያ ስደተኞችን የማስተናገድ ባሕል ለሺህ ዘመናት የኖረ ነው። የዓለም ሀገራት አስገዳጅ የሆነ ሕግ አውጥተው በቁጥጥር ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ባሕል ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፉ ሕግ ተገዢ ሆና ሕጋዊ ስምምነቶችን የፈጸመች እና የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ያወጀች ቢሆንም ስደተኛን መቀበል የጀመረችው ግን ዓለም ሕግ የሚባል ነገር ከማወቁ በፊት ነው። ዛሬ ላይ ያለውን ትውልድ ባሕል ብናስተውል እንኳን አልጋውን ለእንግዳ ለቆ መሬት ላይ የሚተኛ ዜጋ ያለባት አገር ናት። ‹‹ቤት ለእንግዳ ነው›› በሚል የሃይማኖት፣ የባሕልና ሞራል ተገዢ የሆነ ዜጋ ያለባት አገር ናት። የሥልጣኔ እና የሞራል ማማ ላይ ነን የሚሉ የነጭ ሀገራት አፍሪካ አገር ውስጥ የሚደረግን ነገር የማመስገን ልማድ ባይኖራቸውም ስደተኞች ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋሉትን በጎ ነገር በተለያየ አጋጣሚ ሲናገሩ ይሰማል።

አንዳንድ ጊዜ መንገድ ላይ ከሀገር ውስጥ የኔ ቢጤዎች ይልቅ ለውጭ ሀገር ዜጎች ሳንቲም ሲሰጥ ልታስተውሉ ትችላላችሁ። አንዳንድ ሰዎች ምናልባትም ‹‹ለነጭ ማሸቃበጥ›› ሊሉ ይችላሉ። ግን አይደለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞራል ባለቤት ስለሆነ ነው። ለልመና ጎዳና ላይ የወጣ የውጭ አገር ዜጋ ምን እንዳደርግለት ነው የሚሸቃበጥለት? መቼ ውለታ ይመልስልኛል ብሎ ነው?

ለውጭ ሀገር ዜጎች ድጋፍ የሚሰጠው በቁሳዊ ውለታ ሳይሆን ‹‹ነግ በኔ›› በሚለው ብሂል ለሕሊና ተገዢ በመሆን ነው። ያ የውጭ አገር ዜጋ የገንዘብ ችግር ብቻ አይደለም ያለበት፤ የሥነ ልቦና መጎዳትም አለበት። በሰው ሀገር ነው ያለው፤ የሀገሩን አየር ይናፍቃል። ከሀገሩ የወጣበትን ችግር ያስባል። የኢትዮጵያ ሰዎች ለዚህ ሰው ገንዘብ የሚሰጡት በሰው ሀገር ውስጥ ሲኖር በገንዘብም በሞራልም እንደሚጎዳ ስለሚያስቡ ነው። በአጠቃላይ ስደተኛን መቀበል ለኢትዮጵያ ሕጋዊ አስገዳጅ ሳይሆን (ሕጉ እንዳለ ሆኖ) ባሕል ነው ማለት ይቻላል። ይህ ባሕል ደግሞ ዲፕሎማሲ ሆኗል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ገጽታ በበጎ እንዲነሳ ያደርጋል። ይህ ባሕላችን ይቀጥል እያልን ከስደት ጋር የተያያዙ ሌሎች መረጃዎችን በሌላ ክፍል ይዘን እንመለሳለን።

# ዓለም አቀፍ

## የአማዞን መሥራቹ ከድርጅቱ የአራት ቢሊዮን ዶላር አክሲዮኑን ሸጠ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቢሊየነሩ ጄፍ ቤዞስ አማዞን ከተሰኘው ድርጅቱ አክሲዮን አራት ቢሊዮን ዶላር ገደማ የሚሆነውን በቅርቡ መሸጡ ቢቢሲ ዘግቧል።

ግዙፉ የቴክኖሎጂ ኩባንያ አማዞን የተመሠረተው እ.አ.አ 1994 ነው። ኩባንያው ባለንበት ወርሐ የካቲት ቢሊየነሩ የድርጅቱ መሥራች 24 ሚሊዮን የድርጅቱን ድርሻ መሸጡን ይፋ አድርጓል።

የኩባንያው ሊቀ መንበር የሆነው ቤዞስ ለመጨረሻው ጊዜ ከድርጅቱ ድርሻ ቆንጥሮ የሸጠው እ.አ.አ. 2021 ነበር።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የኩባንያው ጉምቱው ቱጃር ከድርጅቱ አክሲዮን 50 ሚሊዮን የሚሆነውን ለገበያ ለማቅረብ እንዳቀዱ አስታውቋል። ይህ የአክሲዮን መጠን በገንዘብ ሲሰላ ስምንት ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይሆናል።

የመጀመሪያው 12 ሚሊዮን የአክሲዮን ድርሻ ለገበያ የቀረበው ባለፈው ሳምንት ዓርብ ሲሆን፣ ሁለተኛው የ12 ሚሊዮን ደግሞ ያለፈው ማክሰኞ ዕለት ለገበያ መቅረቡ ተሰምቷል።

ቤዞስ፤ ዋሺንግተን ግዛት ከምትገኘው ሲያትል ነቅሎ መኖሪያ አድራሻውን ወደ ፍሎሪዳ ግዛት ማያሚ ማድረጉን ባለፈው ዓመት ገልጾ ነበር። ይህ ማለት ቢሊየነሩ ከሚያገኘው ገቢ ምንም ዓይነት ግብር ለመንግሥት አይከፍልም ማለት ነው።

ባለሀብቱ መኖሪያ አድራሻውን የቀየረው ዋሺንግተን ግዛት በርካታ አክሲዮን የሚሸጡ ሰዎች ላይ ግብር መጣሏን ተከትሎ ነው የሚሉ ጭምጭምታዎች ተሰምተው ነበር።


በዋሺንግተን ግዛት ሕግ መሠረት ከአክሲዮን ሽያጭ የሚገኘው ከ250 ሺህ ዶላር በላይ ከሆነ 7 በመቶ የሚሆነውን ለመንግሥት ማስገባት ግዴታ ነው። ግዛቷ ከዚህ ሕግ መጽደቅ በኋላ ባለፈው ዓመት 900 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷ ተሰምቷል።

ጄፍ ቤዞስ መኖሪያ አድራሻውን ባይቀይር ኖሮ ከሚያገኘው አራት ቢሊዮን ዶላር ገቢ 280 ሚሊዮን ዶላር ለመንግሥት ማስገባት ይጠበቅበት ነበር።

ቤዞስ ባለፈው ኅዳር ሲናገር ቤተሰቦቹ ወደ ማያሚ አቅንተዋል፤ ከእነሱ አጠገብ ለመሆን ነው ሲል ለምን ከዋሺንግተን ነቅሎ እንደወጣ አስረድቷል።

ጄፍ ቤዞስ የተወሰነውን የልጅነቱን ዘመኑን ፍሎሪዳ ግዛት አሳልፏል። ብሉ ኦሪጂን የተሰኘው የሕዋ ምርምር ተቋሙ መገኛም እዚያው ፍሎሪዳ ግዛት ነው።

ሀብቱ በገንዘብ ሲሰላ 190 ቢሊዮን ዶላር ይሆናል የሚባልለት ጄፍ ቤዞስ፣ አሁንም የኩባንያው ትልቁ የአክሲዮን ባለድርሻ ነው።



## ጀርመን መጤ ጠሎችን ለመቆጣጠር ያለመ ሕግ ይፋ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጀርመን በሀገሪቱ እየተጠናከረ የመጣውን መጤ ጠል ጽንፈኞችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የሕግ ማዕቀፍ ይፋ አድርጋለች።

ርምጃው በተለያዩ የጀርመን ከተሞች የመጤ ጠል የቀኝ ክንፍ እንቅስቃሴዎችን የሚቃወሙ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፎች ለሳምንታት ከተካሄዱ በኋላ ነው።

ባለፈው ጥር ወር ብቻ በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ የተሠማሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ጀርመናውያን የቀኝ ክንፍ ጽንፈኞችን በመቃወም ወደ ጎዳናዎች ወጥተው ድምፃቸውን አሰምተዋል።

የጀርመን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ናንሲ ፌሰር በተካሄዱት የተቃውሞ ሰልፎች መንግሥታቸው ፖለቲካዊ ርምጃ እንዲወስድ “ማበረታቻና ይሁንታን” እንደሰጠው ገልጸዋል።

ኤኤፍዲ የተባለው ፓርቲ ከፍተኛ አባላትና የኒዮ-ናዚ እንቅስቃሴ ደጋፊዎች የውጭ ሀገር ዜጎችን በጅምላ ከጀርመን ስለማባረር ባለፈው ወር ላይ “በምሥጢር” ስለመወያየታቸው ይፋ መሆኑ በሀገሪቱ ድንጋጤን ፈጥሯል።

“ዴሞክራሲያችንን ለመጠበቅ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የሚየስችሉ ሁሉንም መሣሪያዎች መጠቀም እንፈልጋለን” ሲሉ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሯ ፌሰር ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

“የቀኝ ክንፍ ጽንፈኞችን መረብ መበጣጠስ፣ የገንዘብ ምንጫቸውን ማቋረጥ እና የታጠቋቸውን የጦር መሣሪያዎች ማስፈታት እንፈልጋለን” ብለዋል።

ሚኒስትሯ እንዳሉት 13 ነጥቦችን ያየዘው የሕግ ማዕቀፍ ለጀርመን ማኅበረሰብን ታላቅ ስጋት ሆኖ የቀረቡትን የቀኝ ክንፍ ጽንፈኞችን ለመዋጋት አስፈላጊ ነው።

በሕጉ መሠረት ባለሥልጣናት ጽንፈኛ ቡድኖቹ የሚያዘጋጇቸውን መርሐ ግብሮችን በቀላሉ ለመከልከልና የቡድኑ አንቀሳቃሾችም ከሀገር እንዳይወጡ እና እንዳይገቡ በቀላሉ ለመከልከል የሚያስችል ሥልጣን ይሰጣል።

የጦር መሣሪያ ባለቤትነትን የተመለከተው የሀገሪቱ ሕግም በጽንፈኝነት ተከሰው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ የመንግሥት ሠራተኞችም በቀላሉ ከሥራ የሚባረሩ ይሆናል።

የፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ ቡድኖች የጀርመን መንግሥት በቀኝ ክንፍ ጽንፈኞች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ ለመውሰድ መነሳቱን በበጎ የተመለከቱት ቢሆንም፣ የእንቅስቃሴውን መስፋፋት ለመቆጣጠር ግን እርምጃው የዘገየ ሊሆን ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ተመሳሳይ የሕግ ረቂቅ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረ ሲሆን፣ በሀገሪቱ ምክር ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። አሁን ግን በቀኝ ክንፍ ጽንፈኞች ላይ ሕዝቡ እያሰማ ባለው ተቃውሞ ምክንያት አሁን የቀረበው የሕግ ማዕቀፍ ብዙም ተግዳሮት አይገጥመውም ተብሏል።

የጀርመን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደሚለው በዓመት ውስጥ 20 ሺህ የሚደርሱ የቀኝ አክራሪዎች ወንጀል እና ጥቃቶች የተመዘገቡ ሲሆን፣ እንዲህ አይነቶቹ ክስተቶችም እየጨመሩ ናቸው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን የደመቁበት የዓለም የቤት ውስጥ ውድድር




ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች የበላይነታቸውን እያሳዩ ነው፣

**ቦጋለ አበበ**

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ደረጃ የተሰጣቸው የዓመቱ የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በተለያዩ ከተሞች እየተካሄዱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በነዚህ ውድድሮች በተለያዩ ርቀቶች ከማሸነፍ ባለፈ በአስደናቂ ብቃት በርካታ ፈጣን ሰዓቶችን በማስመዝገብ ደምቀዋል።

ከትናንት በስቲያ በቤልግሬድ በተካሄደው ውድድር የጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል ያፈራት አትሌት ጽጌ ዱጉማ በ800 ሜትር የቦታውን ፈጣን ሰዓት እና ክብረወሰን በማሻሻል አሸንፋለች። አትሌቷ ርቀቱን በ1 ደቂቃ 59 ሰክንድ ከ66 ማይክሮ ሰከንድ በሆነ ሰዓት በማጠናቀቅ ነው የቦታውን ፈጣን ሰዓት እና ክብረወሰን በማሻሻል ያሸነፈችው። በዚሁ ርቀት አትሌት ትግስት ግርማ 2 ደቂቃ ከ21 ማይክሮ ሰከንድ በሆነ ሰዓት በመግባት 2ኛ ደረጃ በመያዝ አጠናቃለች።

ባለፈው ሳምንት በተካሄዱ ውድድሮችም በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በአስደናቂ ብቃት ፈጣን ሰዓቶችን ማስመዝገባቸው ይታወቃል። ከነዚህም መካከል የዓለምና የኦሊምፒክ የ3ሺ ሜትር መሰናክል የብር ሜዳሊያ አሸናፊው አትሌት ለሜቻ ግርማ በ2ሺ ሜትር ፈረንሳይ ሌቪን ላይ ያሳየው ድንቅ ብቃትና ያስመዘገበው ፈጣን ሰዓት ተጠቃሽ ነው።

ለሜቻ በዚህ ውድድር ለረጅም ዓመታት በጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ተይዞ የቆየውን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን ለማሻሻል ከፍተኛ ዝግጅትና ጥረት ቢያደርግም አልተሳካለትም። 4:51:17 በሆነ ሰዓት ውድድሩን ማሸነፍ ቢችልም ያስመዘገበው ሰዓት በታሪክ ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት ሆነ እንጂ ክብረወሰኑን በእጁ ለማስገባት አላስቻለውም። ቀነኒሳ ይህን ክብረወሰን ከዓመታት በፊት 4:49:99 በሆነ ሰዓት ማስመዝገቡ ይታወሳል። ለሜቻ ይህን ክብረወሰን ለማሻሻል ጥቂት ሰከንዶች ቢዘገይም ሌቪን ላይ ያሳየው አስደናቂ አቋም ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል።

በተመሳሳይ ውድድር ሌቪን ላይ የዓለም የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮኗ አትሌት ጉዳፍ ፀጋይ ያሳየችው ብቃትም አስደናቂ ነበር። ጉዳፍ በ3ሺ ሜትር ውድድር የዓለም ክብረወሰን ለማሻሻል የተቃረበች ቢሆንም በሽርፍራፊ ሰከንዶች ሳይሳካላት ቀርቷል። ያም ሆኖ ያስመዘገበችው 8:17:11 ሰዓት የርቀቱ ሁለተኛ ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል። የርቀቱ ክብረወሰን 2014 ላይ ስቶክሆልም ላይ በገንዘቤ ዲባባ የተመዘገበ ሲሆን ሰዓቱም 8:16:60 ነው። በዚህ ውድድር ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሂሩት መሸሻ በ8፡29፡71 የራሷን ፈጣን ሰዓት አስመዝግባ ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። ሌላው የተመዘገበ ድል በቶረን አትሌት ፍሬወይኒ ኃይሉ 1500 ሜትር 3:57.24 በሆነ ሰዓት የገባችበት ነው። እሷን ተከትለውም ድሪቤ ወልተጂና ሂሩት መሸሻ ሁለተኛና ሦስተኛ ሆነው አጠናቀዋል።

የኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮኑ ሰለሞን ባረጋ ወጣቱን አትሌት ቢኒያም መሐሪንና ጌትነት ዋለን በ3ሺ ሜትር አስከትሎ የገባበት ድንቅ ፉክክርም የኢትዮጵያውያን አትሌቶችን የቤት ውስጥ ውድድር የበላይነት ያጎላ ሆናል።

እነዚህ ውጤቶች ከሁለት ሳምንት በኋላ በስኮትላንድ ግላስጎ በሚካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ውድድሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የኢትዮጵያውያንን ስብስብ ከወዲሁ አስፈሪ አድርገውታል። በተለይም በ3ሺ እና 1500 ሜትር የምትወዳደረዋ ጉዳፍ እንዲሁም ለሜቻ ግርማን የመሳሰሉ አትሌቶች በጥሩ ብቃት ላይ ከመገኘታቸው ባሻገር አዳዲስ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እያሳዩ የሚገኙት ድንቅ ብቃት በውጤት መታጀባቸው በዓለም ሻምፒዮናው ኢትዮጵያ ልታስመዘግብ የምትችለውን ውጤት ከወዲሁ እንዲጠበቅ ያደረገ ነው።

በዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አህጉር በሁለቱም ፆታዎች ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። ባለፉት 18 የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች በ17ቱ በመሳተፍ በሜዳልያ ስብስብ ከዓለም 3ኛ ከአፍሪካ 1ኛ ሆና ተቀምጣለች። ኢትዮጵያ በሻምፒዮናው ታሪክ 59 ሜዳሊያዎችንን (31 ወርቅ 13 ብርና 15 ነሐስ) ተገኝተዋል። ባለፉት 18 የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች ላይ የኢትዮጵያ ቡድን በወንዶች ምድብ 23 ሜዳልያዎች (12 ወርቅ 3 ብርና 8 ነሐስ) እንዲሁም በሴቶች ምድብ 30 ሜዳሊያዎች (15 ወርቅ 8 ብርና 7 ነሐስ) ተመዝግበዋል።

ኢትዮጵያ ባለፈው የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮናም ከዓለም አንደኛ ሆና ነበር ያጠናቀቀችው። ይህ የኢትዮጵያ የበላይነት ዘንድሮም በግላስጎ ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ብርቅዬዎቹ አትሌቶች ሰሞኑን እያስመዘገቡ የሚገኙት ፈጣን ሰዓትና የውጤት የበላይነት አንድ ማሳያ ሆኗል።

በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ